# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 275 ሰኔ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# "የአማራና የትግራይ ሕዝቦችን ግንኙነት ለማጠናከር እንሠራለን"

-የሁለቱ ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የአማራና የትግራይ ክልል ሕዝቦችን የእርስ በእርስ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከርና ጥያቄዎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት እንደሚሠሩ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለና የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር ጌታቸው ረዳ ገለጹ።

በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳ የተመራ ልዑክ በባህርዳር ከተማ በመገኘት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ማጠናከር የሚያስችል ውይይት ከአማራ ክልል አመራሮችና የሕዝብ ተወካዮች ጋር አካሂደዋል።

በዚሁ ጊዜ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ

"የአማራና የትግራይ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ሐሳሳ- ከንጉሥ ሰገነትነት እስከ ቱሪስት መናገሻነት

**ልጃለም ፍቅሬ**



ኢትዮጵያ ለቱሪስት መስህብነት የሚውሉ አያሌ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ባለቤት ናት። ቅርሶችን ጠብቆ ለትውልድ ከማስተላለፍ ባለፈ ግን አልምቶ ለቱሪስት መስህብነት የማዋል ልምዱ አገሪቷ ካላት አቅም አንጻር በቂ ነው የሚባል አይደለም።

አሁን አሁን ግን ይህ ልምድ እየተቀየረ ነው፤ ታሪካዊና የተፈጥሮ መስህብ የሆኑ ስፍራዎች በገበታ ለሀገር፣ በገበታ ለትውልድና በሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶች አማካኝነት አልምቶ ለጎብኚዎች ክፍት የማድረግ ልምዱ እየዳበረ ነው።

ምቹ ሁኔታዎች ደግሞ የኢትዮጵያን የመልክዓ ምድሯ አቀማመጥ፣ ነፋሻማ የአየር ንብረት፣ ወብ የተፈጥሮ ገጽታዎች፣ ብርቅዬ እንስሳትና የእጽዋት ዝርያዎች እንዲሁም ቀደምት እውቅ ኢትዮጵያውያን የሠሩት እጅ በአፍ የሚያስጭኑ ዐቢይ ተግባራት ለመጎብኘት ከየትኛውም ክፍለ ዓለማት ከተፍ ማለታቸው የማይካድ ሀቅ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገበታ ለሀገር፣ገበታ ለትውልድ ተብለው እየተሠሩ ያሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ለወጣቱ የሥራ ዕድል ከመፍጠር አልፈው የቱሪዝም ገቢውንም እያሳደጉ መሆኑ ይታመናል።

በተጨማሪም በመንግሥትና በግል ድርጅቶች

ሐሳሳ- ከንጉሥ ሰገነትነት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ማዕከሉ እስካሁን ከ3 ሺህ በላይ የልብ ቀዶ ሕክምና አከናውኗል

## 7ሺህ የልብ ታካሚዎች ወረፋ እየጠበቁ ይገኛሉ

**ማርቆስ በላይ**




አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ከሦስት ሺህ አራት መቶ በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች የልብ ቀዶ ሕክምና ማከናወኑን አስታወቀ።7ሺህ የሚደርሱ ታካሚዎች የማዕከሉን የሕክምና አገልግሎቱን ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውንም አስታውቋል፡፡

በማዕከሉ የልብ ህሙማን ሜዲካል ዳይሬክተርና የጠቅላላ ቀዶ ሕክምና እስፔሻሊስት ሀኪም ዶክተር ሚክሎል መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማዕከሉ ልብ ሳይከፈት በደም ስር ቱቦ ውስጥ የልብ ቀዶ ሕክምና ይሰጣል ያሉት ዶክተር ሚክሎል፤ በማዕከሉ ከ3 ሺህ 4 መቶ በላይ ለሆኑ ታካሚዎች የልብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት መስጠቱን አስታውቀዋል።

በአሁኑ ሰዓት 7 ሺህ የሚደርሱ ታካሚዎች የልብ ታካሚዎች አገልግሎቱን ለማግኘት ወረፋ በመጠበቅ ላይ ናቸው ያሉት ዶክተር ሚክሎል፤ የልብ ሕክምና መገልገያ ዕቃዎች ውድና በቀላሉ

ማዕከሉ እስካሁን ከ3 ሺህ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ልሂቃንና የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራዊ ምክክሩ ሂደት በንቃት ሊሳተፉ ይገባል

ገጽ 2








ዶክተር ኤባ ሚጀና

## የተማሪዎች ምረቃ ከዩኒቨርሲቲ መውጫና ከ12ኛ ክፍል ፈተና ጋር ሳይጋጭ ይከናወናል

### - በ208 የትምህርት ፕሮግራሞች የመውጫ ፈተና ተዘጋጅቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስአበባ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ምረቃ ሥነ-ሥርዓት ከዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና እና ከ12 ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጋር ሳይጋጭ እንደሚከናወን የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በ208 የትምህርት ፕሮግራሞች የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና መዘጋጀቱ ተገልጿል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤባ ሚጀና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ምረቃ፣ ከመውጫና ከ12 ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጋር በማይጋጭ መልኩ እንዲከናወን የሚረዳ ዕቅድ ተዘጋጅቷል።

ዶክተር ኤባ እንዳመለከቱት፤ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ከሐምሌ 3 እስከ ሐምሌ 8 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ይሰጣል። የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ደግሞ ከሐምሌ 17 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ባሉት ቀናት ይሰጣል።

ዩኒቨርሲቲዎች የተማሪዎቻቸውን የምረቃ መርሃግብር ከመውጫ ፈተና በኋላ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲዎቹ ምርጫ የ12ኛ ክፍል ፈተና ሲጠናቀቅ ማካሄድ እንደሚችሉ መገለጹን ጠቁመዋል።

በዘንድሮው ዓመት 180 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና እንደሚወስዱ አስታውቀው፤ ለ208 የመመረቂያ ፕሮግራሞች የሚውሉ የፈተና ዓይነቶች መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

የመውጫ ፈተና የሥርዓተ ትምህርቱ አካል ሆኖ ይቀጥላል ያሉት ዶክተር ኤባ፤ በመሆኑም በተቀመጠው መመሪያ መሠረት ተፈትነው 50 በመቶና በላይ ያመጡ ተማሪዎች እንደሚያልፉ አስረድተዋል፡፡

የመውጫ ፈተናው ሙሉ በሙሉ በኦንላይን የሚሰጥ በመሆኑ የተማሪዎች ስም ዝርዝር ተልኮ ወደ ዳታ ማዕከል መግባቱን አመላክተዋል።

ለተማሪዎች ለፈተና የሚሆን ልዩ የመታወቂያ ቁጥር ይሰጣቸዋል ያሉት ዶክተር ኤባ፤ በተሰጣቸው ቁጥር መሠረት በኦንላይን መፈተን እንዲችሉ የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

በማዕከል ደረጃ የተዘጋጀውን የፈተና ሥርዓት ለመሞከር እንደ አገር ሞዴል ፈተና እንደሚሰጥ አስታውቀው፤ በዚህም ጉድለቶች ካሉ ለማስተካከልና ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

ለፈተናው መሳካት ከኢትዮ ቴሌኮም፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተደራጀ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ብለዋል።

ለመውጫ ፈተናው የሚውሉ ኮምፒዩተሮች፣ የኢንተርኔት አገልግሎትና ጄኔሬተሮች ዝግጅት እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

# ልሂቃንና የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራዊ ምክክሩ ሂደት በንቃት ሊሳተፉ ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአገራዊ ምክክሩ ሂደት ልሂቃን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሁሉም ባለድርሻ አካላት በንቃት ሊሳተፉ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ዶክተር መብራቱ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአገራዊ ምክክሩ አላማ በማያግባቡ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተመካክሮ ችግሮችን መፍታትና ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ ነው፡፡

አገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ደግሞ ልሂቃን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰቦች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ መንግሥት፣ የተለያዩ ማህበራትና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በንቃት ሊሳተፉ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

አገሪቱ በተለያዩ ግጭቶች እንደማለፏ የምክክሩ ፋይዳ የጎላ ነው ያሉት ዶክተር መብራቱ፤ ዕውነተኛ ምክክር ለማድረግ ሁሉን አሳታፊና እና ተጨባጭ ውጤት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው አገራዊ ምክክር ትርክቶችን በማስቆም ዘላቂ ሰላም በማስፈን እንዲሁም በመንግሥትና ኅብረተሰቡ መካከል ያለውን መስተጋብር በማዳበር ረገድ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የጎላ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በሚደረጉት የምክክር መድረኮች ሃሳብን በነፃነት በማንሳትና በሰከነ መንፈስ በመምከር ለአገር የሚበጅ



ዶክተር መብራቱ አለሙ

ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ምሁራን በበኩላቸው በምክክሩ ዙሪያ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን ማዘጋጀት፣ የፌዴራል ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ችግሮችን፣ የተገኙ ውጤቶችን፣ የቀጣይ አቅጣጫዎችን መለየትና አንኳር ሃሳቦችን ማንሳት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በቀጣይ በሚደረገው አገራዊ ምክክር ላይ አንድን ብሔር ጠል ሃሳቦችና ትርክቶችን እንዲቀረፉ ማድረግና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ይገባል ያሉት ዶክተር መብራቱ፤ በምክክሩ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲቆሙ የተጠናከረ ሥራ ማከናወን እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን ያላቸውን በርካታ ጥያቄዎች በአግባቡ ለማስተናገድና በአገሪቱ ያሉ የሀሰት ትርክቶችን መቋጫ ለማበጀት ብሔራዊ ምክክሩ እንደጥሩ አጋጣሚ የሚወሰድ መሆኑን አንስተዋል።

ምክክሩ ሰላምን ከማስፈን ባለፈ ወደፊት አገሪቱ ልትመራበት የምትችልበትን አጀንዳ ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ መላው ሕዝብ ለምክክሩ መሳካት የበኩሉን ሚና ሊወጣ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሂደት ላይ የሃይማኖት ተቋማት፣ ዲያስፖራዎች፣ ግለሰቦችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዜጎች እንደ አገር ምክክር ሊደረግባቸው ይገባል ብለው የሚያምኑባቸውን ጉዳዮች እንዲጠቁሙና ለዚህ አገራዊ ጉዳይ በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ ያቀረበ ሲሆን፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥር 0111261196፤ 0975554500፣ በፖስታ ሳጥን ቁጥር 32623 እንዲሁም በኢሜይል አድራሻ ethiopianndc@gmail.com ጉዳያቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ ማስታወቁ ይታወሳል።

# በመዲናዋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ውጤታማ ሥራ ተከናውኗል

## - በዘንድሮ ክረምት የበጎ ፈቃድ 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ ይሆናሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ የኅብረተሰብ ተሳትፎና የበጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን አስታወቀ። በዘንድሮ የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተገልጿል።

የኮሚሽኑ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሁናቸው ጌትነት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በየዓመቱ ከግንቦት እስከ ግንቦት ወር በ14 ዋና ዋና መርሃ ግብሮች እየተከናወኑ ይገኛል።

በዚህም ከግንቦት ወር 2014 ዓ.ም እስከ ግንቦት ወር 2015 ዓ.ም ድረስ 6 ሺህ 364 ቤቶችን ግንባታና እድሳት በማከናወን ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል ብለዋል።

በበጎ ፈቃድ የቤት ግንባታና እድሳት አገልግሎቱ 30 ሺህ የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ አቶ ሁናቸው አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ሁናቸው ገለጻ፣ በመዲናዋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሦስት ሚሊዮን ዜጎችን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን፤ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ቁጥሩ በአንድ ሚሊዮን አድጓል።

የበጎ ፈቃደኞች የተሳትፎ መጠንና የሀብት አሰባሰብ ሂደቱ እየጨመረ ነው ያሉት አቶ ሁናቸው፤ ባለፈው ዓመት ሦስት ቢሊዮን ብር የነበረው የኅብረተሰብ ተሳትፎ በበጀት ዓመቱ ከስድስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን ገልጸዋል።

ከቤት ግንባታና እድሳት በተጨማሪም በዝቅተኛ



አቶ ሁናቸው ጌትነት

የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ 867 ሺህ 389 የኅብረተሰብ ክፍሎች ማዕድ የማጋራት ሥራ መከናወኑን ገልጸዋል።

ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን የሚወጡ የባለሀብቶች ቁጥር በከተማዋ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ ከ35 ሺህ በላይ ዜጎች በቀን አንድ ጊዜ በምገባ ማዕከላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን ጠቁመዋል።

በተጨማሪ 30 ሺህ 566 ዩኒት ደም በማሰባሰብ፣ 15 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ችግኞችን በመትከልና መንከባከብ፣ ለ68 ሺህ 792 ተማሪዎች የክረምት ማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ መጠናከሩን አስረድተዋል።

እስካሁን በተከናወኑ የበጎ ፈቃድ ሥራዎችም አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን የከተማዋ ነዋሪዎችን በቀጥታ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

የ2015 የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት መጀመሩን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ ሁለት ሚሊዮን በጎ ፈቃደኞችን በማሳተፍ ሦስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ለማሰባሰብ የተቃደ መሆኑን አስታውቀዋል።

በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል አመላክተዋል።

በክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የቤት እድሳትና ግንባታ ይከናወናል ያሉት አቶ ሁናቸው፤ የ3ሺህ 500 የአቅመ ደካማ ቤቶች እድሳትና ግንባታ ይከናወናል ብለዋል።

በተጨማሪም በማዕድ ማጋራት፣ በአደጋ ቅድመ መከላከል፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በትውልድ ግንባታ፣ በጤናና ቀይ መስቀል፣ በፀረ ኤድስ ዘመቻ፣ በመንገድ ትራፊክ፣ በሰላም እሴት ግንባታ፣ በኪነጥበብና መዝናኛ፣ በሙያ በጎ ፈቃድ አገልግሎቶች እንደሚከናወኑ ገልጸዋል።

በበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ የአዲስ አበባን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለሌሎች ከተሞች የማሳየት፣ አገልግሎት የሚበዛባቸውን ተቋማት የማገዝና ማህበራዊ ሚድያ ለበጎ ተግባር የማዋል ሥራዎች እንደሚከናወኑ አስታውቀዋል።

በከተማዋ ተግባራዊ እየተደረገ ለሚገኘው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሁሉም ማህበረሰብ በንቃት ሊሳተፍ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።



አቶ ታምራት ደምሴ

## በክልሉ ለማዕድን ልማት የሚውል ከ19 ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ ቦታ በጥናት ተለይቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በገፀ-ምድርና መልከዓ-ምድራዊ ቅኝት ለማዕድን ልማት የሚውል ከ19 ሺህ 174 ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ ቦታ መለየቱን የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ ታምራት ደምሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ለማዕድን ልማት የሚሆኑ ቦታዎች ተለይተው የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን፣ የብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት የያዘ ክልላዊ ካርታ ማዘጋጀት ተችሏል።

በ2015 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት 20 ሺህ ካሬ ሜትር የሥነ ምድርና የካርታ ጥናት ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በዘጠኝ ወሩ 19 ሺህ 174 ካሬ ኪሎ ሜትር ለማዕድን ልማት የሚሆኑ ቦታዎች መለየታቸውን አስታውቀዋል፡፡

እንደ አቶ ታምራት ገለጻ፣ በተደረገው ቅኝት በአዊ ብሔረሰብ ዞን በአየሁ ጓጉሣ ወረዳ ወይም የኢናባራ - ጎምር 13 ሺህ 57 ካሬ ኪሎ ሜትር የሥነ ምድር ካርታ ጥናት ተደርጓል። በአካባቢው ወርቅ፣ ኦፓል፣ ግራናይት፣ እብነ በረድ፣ ጃስፐር፣ አጌት እና ሌሎችም ማዕድናት ተገኝተው ባለሀብቶችና ወጣቶች እንዲያለሙት እየተደረገ ነው፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን ስማዳ ወረዳ ከ22 ሺህ በላይ ካሬ ኪሎ ሜትር የሥነምድር ጥናትና ካርታ ሥራ ተከናውኖ ኦፓል፣ ኳርትዝ፣ እግኒምብራይት፣ ባዛልትና ሌሎች ማዕድናት መገኘታቸውን አስታውቀዋል።

በአዊ ዞን የጓንጓ ወረዳ 11 ሺህ ስምንት ካሬ ሜትር የሥነምድር ጥናት ተካሂዶ ወርቅ፣ ብረት፣ ግራናይት፣ እብነበረድ፣ ኳርትዝ፣ ጃስፐር፣ አጌት፣ ባዛልትና ሌሎችም ማዕድናት መገኘታቸውን ጠቁመዋል።

በሰሜን ሸዋ ዞን በአንኮበር ወረዳ 693 ካሬ ኪሎ ሜትር ቦታ ላይ በተደረገው የሥነምድር ጥናት ኦፓል፣ ሲናባር (የሜርኩሪ ኦር)፣ ኮፐር፣ ኒኬል፣ ሰልፈር፣ የድንጋይ ከሰል፣ ካኦሊን፣ ራዮላይት፣ የማዕድን ውሃና ሌሎም ማዕድናት መገኘታቸውን ገልጸዋል።

በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ 906 ካሬ ኪሎ ሜትር የሥነምድርና የካርታ ሥራ ጥናት መከናወኑን የጠቆሙት አቶ ታምራት፤ ኮፐር፣ ኒኬል፣ ሰልፈር፣ የድንጋይ ከሰል፣ ሊትየም፣ ኦፓል፣ አጌት፣ ጃስፐር፣ ባዛልት እና ሌሎች ማዕድናት መገኘታቸውን አመላክተዋል፡፡

በዋግ ኽምራ ዞን በሰቆጣ ወረዳ ደግሞ 16 ሺህ 72 ካሬ ኪሎ ሜትር የሥነምድር ጥናትና ካርታ ሥራ ጥናት መከናወኑን ጠቁመዋል። በአካባቢው ብረት፣ ሳንድስቶን፣ ባዛልት፣ ላይም ስቶንና ሌሎች ማዕድናት ተገኝተዋል ብለዋል፡፡

በሰሜን ጎንደር ዞን በጃናሞራ ወረዳ 19 ሺህ 50 ካሬ ኪሎ ሜትር ላይ በተደረገው ጥናት የድንጋይ ከሰል፣ የተለያዩ የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ ባዛልት እንደተገኙ አስታውቀዋል፡፡

በምሥራቅ ጎጃም ዞን በደጀን ወረዳ 621 ካሬ ኪሎ ሜትር ቦታ ላይ የሥነምድርና የካርታ ሥራ ጥናት ተከናውኖ በርካታ ማዕድናት ተገኝተዋል ያሉት አቶ ታምራት፤ በሁሉም አካባቢዎች የተገኙት ማዕድናት የላብራቶሪ ውጤት የማረጋገጥ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡


በክልሉ በተደረገው ጥናት ለማዕድን ልማት የተለዩ ቦታዎችን ለወጣቶችና ለባለሀብቶች የማስተላለፍ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

# የመደመር ትውልድ 12 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ እየተፋጠነ ይገኛል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስአበባ፡- የመደመር ትውልድ በሚል መሪ ሀሳብ በመዲናዋ የተጀመሩ 12 የስፖርት ማዘውተሪያና የሕፃናት መጫወቻ ስፍራዎች ግንባታ እየተፋጠነ መሆኑን የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ገለጸ፡፡

በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የማዕከላት እና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ባዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የመደመር ትውልድ በሚል መሪ ሃሳብ በ11 ክፍለ ከተማዎችና በተጨማሪ አንድ በከተማ ደረጃ በአጠቃላይ 12 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እየተገነቡ ይገኛል፡፡




አቶ ብርሃኑ እንዳመለከቱት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በመደመር መጽሐፍ ሽያጭ ከሚገኘው ገቢ በከተማው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲገነቡ ባስተላለፉት መልዕክት መሠረት ደረጃቸውን የጠበቁ ማዘውተሪያዎች ግንባታ ተጀምሯል።

በመዲናዋ የሚገኙ 41 ቦታዎች ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራነት የተመረጡ መሆኑን ጠቁመው፤ በመጀመሪያ ዙር 12 የስፖርት ማዘውተሪያዎች ግንባታ በተሻለ ፍጥነት እየሠተሩ መሆኑን አስታውቀዋል።

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎቹ የሕፃናት የስፖርት ማዘውተሪያና መጫዎቻዎች የተካተቱበት ሲሆን፤ የቅርጫት ኳስ፣ የእጅ ኳስና መረብ ኳስ ስፖርት አገልግሎቶችን ያካተተ ሜዳ እንደሚኖራቸው አቶ ብርሃኑ አስረድተዋል።

በተወሰኑ የስፖርት ማዘውተሪያዎች የእግር ኳስ ሜዳ እንደሚገነባ ገልጸው፤ ወጣቶች ያሉባቸውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ችግር ለመቅረፍ ሰፊ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

የማዘወተሪያ ስፍራዎቹ ግንባታ መጋቢት ወር 2015 ዓ.ም በከንቲባ አዳነች አቤቤ የተጀመሩ ሲሆን፤ የግንባታ ሂደታቸው በአማካይ 40 በመቶ መድረሱን አቶ ብርሃኑ ገልጸዋል።

አቶ ብርሃኑ እንዳስታወቁት፤ ግንባታዎቹ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ እንደሚጠናቀቁ ይጠበቃል።

ከመደመር ትውልድ የስፖርት ማዘውተሪያ ፕሮጀክቶች በተጨማሪ በ2015 ዓ.ም ግንባታቸው ከተጀመሩት 29 የስፖርት ማዘውተሪያዎች ከ10 በላይ የሚሆኑት አጠቃላይ ግንባታቸው ተጠናቋል ብለዋል።

በዘንድሮ በጀት ዓመት የተለያዩ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ለመገንባት 340 ሚሊዮን ብር በጀት በመያዝ ለከተማ አስተዳደሩ መቅረቡን ገልጸዋል።

አቶ ብርሃኑ እንደገለጹት፤ በዘንድሮ ዓመት ከተጀመሩት 29 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከ10 በላይ የሚሆኑት ግንባታቸው የተጠናቀቀ ሲሆን 12 የእግርኳስ ሜዳዎች ደግሞ የግንባታ ሂደታቸው ከ52 በመቶ በላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

በ2015 በጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በግል ባለሀብቶች እገዛ ለ26 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ዕድሳት ተከናውኗል።



ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ የውሃ ፕሮጀክቶች ወደሥራ ገብተዋል



አቶ አዳነ ተክለጊዮርጊስ

# በከተማዋ 120 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ያደረጉ የውሃ ፕሮጀክቶች ሥራ ጀመሩ

**አማን ረሺድ**

ሻሸመኔ፡- በከተማዋ 120 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ያደረጉ የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ሥራ መጀመራቸውን የሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የሻሸመኔ ከተማ ከንቲባ አቶ አዳነ ተክለጊዮርጊስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ በ88 ሚሊዮን ብር ወጪ በተለያዩ አካባቢዎች ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን በማስቆፈር የውሃ አቅርቦት ችግሩን ቀርፏል።

እንደ አቶ አዳነ ገለጻ፤ በሻሸመኔ ከተማ ከዚህ ቀደም በ15 ቀን በፈረቃ ሲቀርብ የነበረው የመጠጥ ውሃ አሁን ላይ በየቀኑ ለተጠቃሚዎች ማድረስ ተችሏል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ይነሳ የነበረውን የውሃ መሠረተ ልማት አቅርቦት ጥያቄ ምላሽ መስጠት የሚያስችል ሥራ ተከናውኗል ያሉት ከንቲባው፤ ፕሮጀክቶቹ ወደሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ያደረጉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ምስጋና ይገባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የውሃ ፕሮጀክቶቹ ወጪ ግማሹን በኅብረተሰቡ የውሃ ቆጣሪ ክፍያ ላይ ጭማሪ ተደርጎ የሚሸፈን መሆኑን አስታውቀው፤ ቀሪው ወጪ በከተማ አስተዳደሩ የሚሸፈን መሆኑን አቶ አዳነ አስረድተዋል፡፡

ከጥልቅ የውሃ ጉድጓዶቹ እስከ ተጠቃሚው ኅብረተሰብ የተዘረጋው የውሃ መስመር ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መገንባቱን ከንቲባው ገልጸዋል።

የውሃ ፕሮጀክቶቹ ወደሥራ በመግባታቸው ኅብረተሰቡ በንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ምክንያት ይደርስበት የነበረውን የጤናና ተያያዥ ችግሮች ለመቀነስ የሚረዳ መሆኑን ከንቲባው አመላክተዋል።

ከከተማው ዕድገትና የሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ለሁሉም ሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ የሚከናወኑ ሥራዎች ቀጣይነት እንዳላቸው ጠቁመዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የኅብረተሰቡን ተያያዥ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ለመፍታት በትኩረት እንደሚሠራ አቶ አዳነ አመላክተዋል።

በከተማው በሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎች ላይ ኅብረተሰቡ ይበልጥ ተሳታፊ እንዲሆን ከንቲባው ጥሪ አቅርበዋል።

# በመዲናዋ የድምጽ ብክለት ባስከተሉ 208 ተቋማት ላይ የተለያየ ርምጃ ተወሰደ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የድምጽ ብክለትን ባስከተሉ የንግድ ተቋማት ላይ የተለያየ ርምጃ መወሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ድዳ ድሪባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በከተማው በተለያየ ቦታ ከተገቢው በላይ ድምጽ በመጠቀም የከተማዋን ሰላምና ጸጥታ በሚያውኩ የንግድ ተቋማት ላይ ርምጃ እየተወሰደ ነው፡፡

እንደ አቶ ድዳ ገለጻ፤- በከተማዋ አዋኪ ድምጾችን የመለየት ቁጥጥር ከተጀመረ በኋላ 423 ቤቶች ላይ ድምጽ ተለክቶ ከዚህም ውስጥ 208ቱ ሕጉን ተላልፈው በመገኘታቸው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። ስድስት የንግድ ቤቶች ደግሞ ሙሉ በሙሉ እንዲታሸጉ ተደርጓል።

ርምጃ የተወሰደባቸው የንግድ ተቋማቱ በከተማው በሚፈጠሩ አዋኪ ድምጾች ምክንያት የነዋሪውን የመኖር መብት እየተጋፉና ኅብረተሰቡን ለተለያየ ችግር ሲዳርጉ እንደነበር አስታውሰዋል።

የድምጽ ብክለትን ለመከላከል የሚረዳ ዘመናዊ የድምጽ መለኪያ መሣሪያ ከውጭ አገር ተገዝቶ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል።

በከተማዋ የድምጽ ብክለትን ችግር ለመቀነስ በሁሉም ክፍለ ከተሞች የድምጽ መለኪያ ማሽኖች ተገዝተው ጥቅም ላይ መዋላቸውን ሥራ አስኪያጁ ጠቁመዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ በመለኪያ መሣሪያ መሠረት ከ45 ዴሲ. በላይ ድምጽ በሚያሰሙ የንግድ ተቋማት ላይ የመጀመሪያ ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫና ዳግም ሕግ እንዳይጥሱ የደብዳቤ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል፡፡

የድምጽ ልኬቱ በአካባቢው ላይ ምን ያህል ነዋሪውን ሊረብሽ እንደሚችል ለማወቅ ከንግድ ቤቶች ውጪ የሚለካ መሆኑን አስረድተዋል።

አቶ ድዳ እንዳስታወቁት፤ የድምጽ ብክለቱ በከተማዋ ከቀን ይበልጥ በምሽት ጊዜያት ጎልቶ ይስተዋላል። ችግሩን ለመቀነስ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ከሚመለከታቸው የጸጥታ አካላት ጋር አስፈላጊውን የቁጥጥር መሣሪያና ባለሙያ መድቦ እየሠራ ይገኛል።

በከተማው በተለይ ብዙ ሰው በሚገኙባቸው አካባቢዎች የመንገድ ዳር ንግድ ቦታዎች ላይ አዋኪ ድምጽ በሰፊው ይስተዋላል ያሉት አቶ ድዳ፤ በተወሰነ መልኩ በሃይማኖት ተቋማት አካባቢ ከፍተኛ ድምጽ የመጠቀም አዝማሚያ መኖሩን ገልጸዋል።

የንግድ ተቋማትና ግለሰቦች የድምጽ ብክለት በከተማዋ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመገንዘብ ባለሥልጣኑ ያወጣውን ሕግ በማክበር እንዲሠሩ ሥራ አስኪያጁ ጥሪ አድርገዋል፡፡


አቶ ድዳ ዲሪባ

## “የአማራና የትግራይ ሕዝቦችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳ በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሠረት በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የወንድማማችነት ስሜት ማስቀጠል እንደሚገባ ገልጸዋል።

«የሕዝባችን ፍላጎት ሰላም ነው፣ የሕዝባችን ፍላጎት ተከባብሮ መኖር ነው፣ አብሮ መነገድ ነው» ያሉት አቶ ጌታቸው፤ የሕዝቦች የቀደመ ግንኙነት እንዲመለስ የመሪዎች ቁርጠኝነት ያስፈልጋል ብለዋል።

«ባህር ዳር መገኘታችን የተከፈተውን በር አስፍተን፣ ሁሉም ዓይነት ሰላማዊ እንቅስቃሴ በሁለቱም ወገን የሚካሄድበት ሁኔታ ለመፍጠር ነው» ብለዋል።

የመገናኛ ብዙኃንም ጥላቻን ሳይሆን ሰብዓዊነትን መሠረት አድርገው መሥራት እንዳለባቸው ያሳሰቡት አቶ ጌታቸው የአማራ ክልል አመራሮችም የሁለቱ ክልል ሕዝቦች ወደ ቀደመ ግንኙነታቸው እንዲመለሱ እያደረጉ ላለው እንቅስቃሴ ምስጋና አቅርበዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው ሕዝብ ሰላምን አጥብቆ እንደሚፈልግ ገልጸው፣ ለሁሉም ነገር መሠረቱ ሰላም መሆኑን ተናግረዋል።

የአማራ ክልል አመራር ከሕዝቡ ጋር በመሆን የሁለቱ ክልሎች ሕዝቦች ሰላምና በጋራ አብሮ ማደግ በትኩረት እንደሚሠራ አስረድተዋል።

በሁለቱ ክልሎች መካከል ትራንስፖርት ተጀምሮ ሕዝብ ለሕዝብ መገናኘትና አስፈላጊው የንግድ ልውውጥ መካሄድ እንደሚገባው አስረድተዋል።

ይህ እንዲፋጠን ደግሞ አሁን ላይ ሕዝብን እየመሩ ያሉ የሁለቱ ክልል አመራሮች ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

ዛሬ የተደረገው ግንኙነት የመጨረሻ ሳይሆን በየደረጃው መውረድ የሚገባውና ለዘመናት በጋራ የኖሩትን የሁለቱን ክልል ሕዝቦች ግንኙነት ወደነበረበት ለመመለስ ያለመ ነው ብለዋል።

በአማራ ክልል በኩል የሕዝቦች ግንኙነት ወደነበረበት እንዲመለስ አስፈላጊው ሥራ ሁሉ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር አመራሮች የሁለቱ ክልል ሕዝቦች ግንኙነት ወደነበረበት እንዲመለስና የተጀመረው የሰላም ግንኙነት የፀና ለማድረግ ባህር ዳር መጥተው ውይይት በማድረጋቸው ምስጋና አቅርበዋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው የክልሎቹ አመራሮች የተጀመረውን ሰላም ማጽናትና ለሕዝቦች አንድነት መትጋት አለባቸው ብለዋል።

ከውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል ወይዘሮ የሕዝቡ ጥላካሳ ለሕዝቦች በጋራና በሰላም አብሮ መኖር በክልል መሪዎች የተጀመረው ሰላም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከልብ በመነጨ መንገድ መሥራት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

የአማራና የትግራይ ሕዝብ በዘርፈ ብዙ መስተጋብሮች ለዘመናት ተሳስሮ የነበረና ወደ ፊትም አብሮ የመኖር እጣ ፈንታ ያለው እንደሆነ የገለጹት አቶ ስማቸው ንጋቱ ናቸው።

«ለዘመናት ተሳስሮ የኖረን ሕዝብ መበጠስ አይቻልም» ያሉት አቶ ስማቸው መሪዎች የሕዝቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

በተያያዘ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ወደመቀሌ ተጉዘው ሲመለሱ የትግራይ ክልልን መልሶ ለማቋቋም የሚያግዝ የ510 ሚሊዮን ብር ድጋፍ አስረክበናል ሲሉ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

«ሰላምን እናፅና !» ብለን በትግራይ ባደረግነው ጉብኝት የወገኖቻችንን ችግር በመካፈል የጎደለውን ሞልተን ከችግሮቻቸው ማዶ ያለውን ብሩህ ተስፋ አሻግረው እንዲመለከቱ ለማድረግ እና ወገን እንዳላቸው ለማሳየት ድጋፍ ለማድረግ በገባነው ቃል መሠረት፣ የከተማችንን ባለሀብቶችና ነዋሪዎች በማስተባበር 510 ሚሊዮን ብር የሚገመት ድጋፍ አድርገናል ብለዋል።

ድጋፉ የምግብ ቁሳቁስ፣ የሕክምና ማዕከላትን አገልግሎት ለማስጀመር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የሕክምና ቁሳቁሶችን፣ የትምህርት መሣሪያዎችን፣ ለተፈናቃዮች የሚውሉ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የትናንት ችግሮቻችንና ፈተናዎቻችንን ዛሬ በፍቅር እየፈታን፣ ቀጣዩ ትውልድ ከቁርሾ ይልቅ ሰላምን፤ ከቂምና በቀል ይልቅ ፍቅርን እያስቀደምን ሕዝቦች በመተሳሰብና በፍቅር የሚኖሩባት አገር መገንባታችንን እንቀጥላለን ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

## ሐላላ- ከንጉሥ ሰገነትነት እስከ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲሁም በግል ባለሀብቶች እየተገነቡ የሚገኙት ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ፓርኮችና የወጣቶች መዝናኛዎች ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ እየሆኑ ነው።

የገበታ ለሀገር አንዱ አካል የሆነው የሐላላ ኬላ ሪዞርትም በአገሪቱ አዲስ ለቱሪስት መዳረሻ ከሆኑ ውብና ማራኪ ስፍራዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

ሐላላ ኬላ ሪዞርት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ዳውሮ ዞን ከአዲስ አበባ በ450 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

ቦታው ተፈጥሮን በልኩ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን፤ ሐላላ ኬላ የሚለውን ስያሜ ያገኘው በ1760 ዓ.ም እንደተወለዱ ከሚነገርላቸው በቀድሞ የዳውሮ ንጉሥ ሐላላ አማካኝነት እንደሆነ ይነገርለታል፡፡

ንጉሡ ያስገነቡት የድንጋይ ካብና ሰገነት አሁን ላይ የቱሪስቶች መናገሻ እየሆነ ይገኛል። በኮይሻ የኃይል ማመንጫ አማካኝነት ከተፈጠረው ሰው ሰራሽ ሐይቅ ዳርቻ የሚገኘው የሐላላ ኬላ ሪዞርት በውስጡ የአካባቢውን ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የሚያሳይ ሙዚየሞች እንዲሁም የምርምር ማዕከላት አካቶ ይዟል።

ሐላላ ኬላ ሰላምንና ጸጥታን፣ ታሪክና ባህል ለሻቱ እንዲሁም ተፈጥሮን ከልባቸው ለሚያደንቁና በፍሬውም ደስ ለሚሰኙ ጎብኚዎች የቅርብ ወዳጅ ሆኗል፡፡

ቦታው ታላቁ የዳዉሮ ግንብ ካቲ ሐላላ፣ አስደናቂው ኮይሻ የኃይል ማመንጫና ልብን በሃሴት የሚሰውረው ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ እንዲሁም በተለያዩ ባህሎች የበለጸገው ፃራ ማህበረሰብ የሚገኝበት ውብ ስፍራ ነው፡፡

የሐላላ ኬላ ሪዞርት ለቱሪስት መዳረሻ መሠረተ ልማት ምቹ ሆኖ ከመሠራቱም በተጨማሪ የአካባቢው የመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ ታሪካዊ ቦታዎች፣ በዙሪያው የሚገኙ የተለያዩ ዓይነት የዕፅዋት ዝርያዎች ጎብኚው ወደ ስፍራ እንዲነጉድ የሚያስገድዱ ትልቁ ምክንያቶች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ የቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም፤ በገበታ ለሀገርና በገበታ ለትውልድ እየተሠሩ ያሉ የቱሪዝም የልማት ሥራዎች የቱሪዝም ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ናቸው ይላል፡፡

የገበታ ለሀገር አንዱ አካል የሆነውን የሐላላ ኬላ አገሪቱንም ሆነ ክልሉን የቱሪስት መዳረሻ ከማድረግ አኳያ ለዚህ አንዱ ማሳያ መሆኑን ነው የተናገረው።

የኮይሻ ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ ከሚሰጠው የኤሌክትሪክ አገልግሎት በተጨማሪ የተፈጠረው ሰው ሰራሽ ሐይቅ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ለቱሪዝም ልማት ማዋል እንዲሁም ትኩረት ተነፍጎት የነበረው የሐላላ ኬላ ለምቶ የቱሪስት መዳረሻ መደረጉ እሰየው የሚያስብል ተግባር ነው ይላል፡፡

እንደ ጋዜጠኛ ሄኖክ ከሆነ፤ የሐላላ ኬላ ሪዞርት በአካባቢው መገንባቱ የቱሪስት የቆይታ ጊዜ ያራዝማል፤ የአካባቢውን ማኅበረሰብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ያደርጋል።

ቦታው የረጅም ዘመን ታሪክ ያለውና የአካባቢው ቱባ ባህል የያዘ ነው ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ የተገነባው ሪዞርት ዓለም አቀፍ የጎብኚዎች ማረፊያ መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አገሪቱን የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያስረዳል።

ልማቱ ቱሪዝሙን ከማስፋፋትና የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት የመሳብ ዕድል እንዳለው ይጠቁማል።

ልማቱ አሁን ከሚኖረው ከፍተኛ ጠቀሜታ በላይ ቀጣይ ለሚሠሩ ልማቶች ትልቅ መነቃቃት የሚፈጥር ነው የሚለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ ቱሪዝምንና ተፈጥሮን የመጠበቅ ባህል የበለጠ እንዲጠነክርና እንዲያድግ ያደርጋል ብሏል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ቦታዎች መጎብኘትና የቱሪስት መዳረሻዎች መሆን እየቻሉ በመንገድ መሠረተ ልማት እጦት ብቻ መዳረሻ ሳይሆኑ ቀርተዋል የሚለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ ሐላላ ኬላ ግን የመንገድ መሠረተ ልማት ችግር የተቀረፈለት መሆኑ ለጉብኝት አመቺ መሆኑን ያስረዳል።

ኢትዮጵያ ብዙ የቱሪዝም ሀብቶች ቢኖሯትም በቱሪስም ልማት ምክንያት ለዓለም ገበያ የቀረቡት ግን ውስን መሆናቸው ሥራውን ማጠናከር ይገባል ሲል ጋዜጠኛ ሄኖክ ሃሳቡን ሰጥቷል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በበኩላቸው ሐላላ ኬላ ሪዞርት ተገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ከሆነ በኋላ የተለያዩ አገር ዜጎች ቦታውን እየጎበኙ መሆኑን ያስረዳሉ።

በተለይ በአዲስ አበባ የሚኖሩ የወጭ አገር ዲፕሎማቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ ቦታው እየሄዱ ነው የሚሉት አቶ ስለሺ፤ ሪዞርቱ በአካባቢው ያሉት ታሪካዊ ቅርሶችና የማኅበረሰቡን ቱባ ባህል በማስተዋወቅ ረገድ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል ይላሉ።

የዳውሮ ዞን በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህብ ያለው ቢሆንም በብዙዎች ዘንድ ሳይታወቅ መቆየቱን አስታውሰው፤ ፕሮጀክቱ ከተመረቀ በኋላ ቦታው ያለው የቱሪዝም አቅም እየታወቀ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በአገራችን ለቱሪስት መስህብ የሚሆኑ ብዙ ቦታዎች አሉ የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተለያዩ መሠረተ- ልማት ችግሮች ምክንያት መዳረሻ መልማት አልቻሉም። ሐላላ ኬላ ዕምቅ ሀብቶቻችንን እንዴት ማልማት እንደምንችል ማሳያ ይሆናል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን ሐላላ ኬላ ሪዞርትን በመጎብኘት ከባህልና ታሪካቸው ጋር ይበልጥ ቁርኝት ሊፈጥሩ ይገባል ሲሉ አቶ ስለሺ ተናግረዋል።

## ማዕከሉ እስካሁን ከ3 ሺህ

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የማይገኙ መሆናቸው አገልግሎቱን በስፋት ለመስጠት አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ሰዓት አስፈላጊ ግብዓቶች በመገኘታቸው የሕክምና አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል፡፡

ማዕከሉን በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች የማይሰጡ ውስብስብ የልብ ቀዶ ሕክምናዎችን በነፃ መሥራቱ ከሌሎች ሆስፒታሎች ለየት ያደርገዋል ብለዋል፡፡

ማዕከሉ ከተቋቋመ 30 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን፤ የልብ ቀዶ ሕክምና ታካሚዎች በውጭ አገር በሚገኙ ሆስፒታሎች እንዲታከሙ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰዋል።

ዶክተር ሚክሎል እንዳመለከቱት፤ ከ15 ዓመታት በፊት ማዕከሉ የራሱ ሕንፃ ተገንብቶለት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ካለፉት ሰባት ዓመታት ወዲህ ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ሀኪሞች የልብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል።

በአሁኑ ሰዓት በማዕከሉ ሁለቱን ዓይነት አገልግሎቶች እየተሰጠ ይገኛል ያሉት ዶክተር ሚክሎል፤ ለታካሚዎች ክትትል የማድረግና በዘመናዊ መሣሪያዎች የታገዘ የልብ ቀዶ ሕክምና እየተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል።

የአገልግሎቱን ተደራሽነት ለማስፋትና ከቀን ወደ ቀን ለማሻሻል የሚረዱ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል። በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በሳምንት ሁለት ቀን ይሰጥ የነበረውን የቀዶ ሕክምና አገልግሎት በሳምንት አራት ጊዜ እየተሰጠ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ለማዕከሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት፣ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችና ግለሰቦች ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ገልጸው፤ የማዕከሉን አገልግሎት ለማስፋት የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት የሚያስፈልግበት ወሳኝ ወቅት!

ኢትዮጵያ የምታስመዘግበውን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ተከትሎ እንዲሁም ዕድገቱን ለማስመዝገብ በምታከናወናቸው ተግባራት በኮንስትራክሽን ዘርፉ በኩል ለውጦች ሲመዘገቡ ቆይተዋል። ይህም ስኬት አገሪቱን ግንባታ እንደ አሸን የፈላበት በመባል በውጭው ዓለም ጭምር እስከመታወቅ አድርሷትም ነበር፤ ይህን ግንባታ የሚያከናውነው የኮንስትራክሽን ዘርፉም እንዲሁ በተለይ በተቋራጮች፣ በአማካሪዎችና በባለሙያዎች በኩል በተሰጠው ልዩ ትኩረት ከቁጥር አኳያ ከፍተኛ ስፍራ ላይ መድረሱንም የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ይመሰክራሉ።

በአገሪቱ በመንግሥት ባለቤትነት የሚገነቡት የኃይል ማመንጫዎች፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ የፍጥነት መንገድን ጨምሮ የሚገነቡ ሌሎች የመንገድ መሠረተ ልማቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ አየር ማረፊያዎች፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የጤና ተቋማት፣ የባቡር መስመሮች፣ የቱሪዝም መሠረተ ልማቶች፣ ወዘተ እንዲሁም የከተሞች መስፋፋትና አዳዲስ ከተሞች መፈጠር ሲታሰብ አገሪቱ በርግጥም ኮንስትራክሽን የተስፋፋባት ስለመሆኗ ጥሩ ማሳያዎች ተደርገው ይወሰዳሉ። በዚህ ላይ የግሉ ዘርፍ የሚያካሂዳቸው የሪል ስቴት፣ የሆቴል፣ የኢንዱስትሪና የመሳሰሉት ግንባታዎች ሲታከሉ ሁኔታው በርግጥም ኮንስትራክሽን እንደ እንጉዳይ የፈላባት ያስብላታል።

ይህ ዘርፍ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባጋጠሙት ተግዳሮት ለመቀዛቀዝ ተዳርጓል። እንደ ሲሚንቶ ባሉ የግንባታ ግብአቶች እጥረት፣ በፋይናንስ እጦት፣ በተወዳዳሪነት አቅም ማነስ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃና በአገሪቱ ተከስቶ በነበረው የኮቪድ ወረርሽኝ እንዲሁም በሰላም እጦት ሳቢያ የግንባታው ኢንዱስትሪ በሚጠበቅበት ስፍራ ላይ አይደለም፤ ተጎድቷል። ግንባታዎች ከፋኛ መጓተት፣ የግንባታ ወጪዎች በየቀኑ መናር፣ የአገር ውስጥ ተቋራጮች በዘርፉ ውስጥ ራሳቸውን ማቆየት እየተሳናቸው መምጣትም ይህንኑ ያመለክታሉ።

እየተቀዛቀዘ ያለው ደግሞ በፍጹም መቀዛቀዝ የሌለበት ግዙፍ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ነው። ለአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት 19 በመቶውን ያበረከተ፣ ከአገሪቱ የካፒታል በጀት ከ60 እስከ 65 በመቶውን የሚያንቀሳቅስ እንዲሁም ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከግብርናው ቀጥሎ ትልቁን ድርሻ የያዘ ዘርፍ ነው የተቀዛቀዘው።

የዚህን በአገር ምጣኔ ሀብት ላይ ጉልህ ሚና የሚጫወት ግዙፍ ዘርፍ ችግሮች ከስር ከስር መፍታት በተገባ ነበር። ግን ያን ማድረግ አልተቻለም፤ በተቋራጮች በኩል ተወዳዳሪ ተቋራጭ ለመገንባት ዕቅድ ቢያዝም ተቋራጮች ተወዳዳሪ መሆን አይደለም ራሳቸውን ዘርፉ ውስጥ ማቆየት እየተቸገሩ መሆናቸው እየተጠቆመ ነው። በአጠቃላይ ይህ ኢንዱስትሪ መታመሙ፣ ያለተተኪ እየቀረ መሆኑ እየተገለጸ ነው።

ስለሆነም ኢንዱስትሪውን መታደግ የግድና የግድ ይሆናል። የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርም የዘርፉን ችግሮች እያዳመጠ ለመፍትሄ እየሠራ ይገኛል። አዲስ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ለመቅረጽ እየተዘጋጀ ነው። ለዚህ የፖሊሲ ሰነድ ግብዓት ለማሰባሰብም ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር እየመከረ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ሚኒስቴሩ በቀጣይ የተለያዩ የአሠራር ማሻሻያዎችን እንደሚተገብርም ይጠበቃል።

የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት በፖሊሲ ማሻሻል ጭምር እያከናወነ ያለው ተግባር ይበል የሚያሰኝ ነው። አሁን የፖሊሲ ሰነዱን ለማዳበር ግብዓት እያሰባሰበ ያለበት ሁኔታ ባለድርሻዎችን በማሰባሰብ ጠንካራ የጥናት ሰነዶችን በማዘጋጀትና በማወያየት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

አገር እንዳለፉት ወቅቶች ሁሉ በምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ ትገኛለች። ይህንንም ዓለም አቀፉ ተቋም አይኤም ኤፍ ጭምር አረጋግጦታል። በተለያዩ ዘርፎች እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትና በአገሪቱ እየሰፈነ የመጣው ሰላም የምጣኔ ሀብት ዕድገቱን ዘላቂነት ይጠቁማሉ። በዚያው ልክ የግንባታው እንቅስቃሴም ይቀጥላልና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለዚህ በሚመጥን መልኩ ዝግጁ ማድረግ ይገባል። ዘርፉን ለመታደግ የሚከናወነው ተግባር ችግሮቹን ብቻ የሚፈታ ሳይሆን ቀጣይ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል።

በተለይ በአገር በቀል ተቋራጮች ተወዳዳሪነት እንዲሆኑ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል። በአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ የአገር በቀል ተቋራጮችን የተወዳዳሪነት አቅም በመገንባት ከዘርፉ ገበያ ድርሻ 75 በመቶውን፣ ከምሥራቅ አፍሪካ የዘርፉ ገበያ ደግሞ 25 በመቶውን እንዲይዙ መታቀዱ ይታወቃል። ይህን ዕቅድ ለማሳካት ተቋራጮችን ተወዳዳሪ ማድረግ ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል።

አሁን ያለው የተቋራጮች የተወዳዳሪነት አቅም ቀጣዩን ኃላፊነት መሸከም የሚችል ስላለመሆኑ በቂ ግንዛቤ ተይዞበታል። የውጭ የግንባታ ተቋራጮች ወደ አገሪቱ እንዲመጡ ከተደረገበት ሁኔታም ይህንኑ መገንዘብ ይቻላል። አገሪቱ በፍጥነት የሚሠራ ግዙፍ ፕሮጀክት ይዛ ብትመጣ ይህን ሊሠራ የሚችል የአገር ውስጥ ተቋራጭ መገኘት መቻሉ አጠራጣሪ ስለመሆኑ እየተገለጸ ነው። ይህ ትልቅ ክፍተት መሆኑ ሊታወቅ የግድ ይሆናል።

ዘርፉን የሚመራው አካል አሁን የተቋራጮችን ተወዳዳሪነት አቅም ለመገንባት ቁርጠኛ ሆኗል። የአገሪቱ ተቋራጮች ግዙፍ የሚባሉትን የግንባታውን ዘርፍ ፕሮጀክቶች ለመገንባት ጭምር ዝግጁ መሆን አለባቸው። የበይ ተመልካች ሆነው መቆየት የለባቸውም። ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የተወዳዳሪነት አቅምን በማጎልበት ነው።

ትላልቆቹ ተቋራጮች የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሥርዓታቸውን በመቀየር የኮርፖሬት ባህል እንዲገነቡ መንግሥት እየጠየቀ ነው። ትናንሾቹን ተቋራጮች ደግሞ እየደገፈ ለማብቃት እንደሚሠራ አስታውቋል። የተወዳዳሪነት አቅም መጎልበት ከአገርም አልፎ በምሥራቅ አፍሪካ ጭምር መቀጠል እንዳለበት ታምኖበት እየተሠራ ነው። ተቋራጮች ይህን የመንግሥት ቁርጠኝነት ለመጠቀም ዝግጁና ቁርጠኛ ሊሆኑ ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

ኢፕድ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናን በስኬት ለመወጣት

ዳንኤል ዘነበ

" ሰዎች ወደዚህች ዓለም ሲመጡ አራት ዝንባሌዎችን ይዘው ይመጣሉ። እነርሱም የምጣኔ ሃብት ዝንባሌ (Homo Economicus)፣ የኃይማኖተኝነት ዝንባሌ (Homo Religious)፣ የፖለቲከኛነት ዝንባሌ (Homo Politicus) እና የንድፈ-ሃሳብ ዝንባሌ (Homo Theoreticus) ናቸው። ስለዚህ የአንድ መምህር ተግባሩ ዝንባሌዎቹን ከተማሪው ውስጠ-ልቡና ፈልፍሎ ማውጣት ይሆናል ”

ዶክተር እጓለ ገብረ ዮሐንስ ‹‹የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ›› በሚል ርዕስ በ1956 ለንባብ ባበቁት መጽሐፍ ላይ ስለ ትምህርት አስፈላጊነትና ፋይዳ ያስቀመጡት ሃሳብ ነው። ከላይ በመንደርደሪያነት ያነሳኋቸው የሊቃውንቱ ሐሳብ የመምህር እና የትምህርትን ወሳኝነትና ከፍተኛ ፋይዳ የሚያሳይ፤ የአንድ አገር እድገት ቁልፍ ያለው በትምህርት ዘርፍ ላይ መሆኑንም የሚጠቁም ነው።

ባለፉት ሁለት አስርቶች በአገራችን ለትምህርት ተደራሽነት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እንደተሰራ ይነገራል። ለአብነት በአሁን ወቅት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጥር ሃምሳ ሊደርሱ ተቃርበዋል። በግሉ ዘርፍም 150 ስለመድረሳቸው መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተሰራው ስራ ከጥራት አንጻር ሲመዘን ግን ውጤቱ አንገት የሚያስደፋ ስለመሆኑ በተጨባጭ የሚታይ ነው።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በአንድ ወቅት፣ ስለ ትምህርት ጥራት "...የትምህርት ተደራሽነት ማደጉን ሳንረሳ፣ ዘርፉ በእጅጉ በመጎዳቱ ላይ ግን ምንም ክርክር አይኖርም፡፡ በመሠረታዊነት ትምህርትን ማዳረስ አስፈላጊ ቢሆንም፤ ነገር ግን በቂ የትምህርት መሣሪያ፣ አስተማሪና የትምህርት አሰጣጥን ሳይፈጥሩ ሕንፃ እየገነቡ ብቻ ተማሪዎችን መሰብሰብ ችግሩን እንዲፈጠር አድርጓል " ሲሉ መናገራቸውን አስታውሳለሁ፡፡

በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓቱ የቁልቁለት መንገድ ከታች ከመሰረቱ ጀምሮ እስከ ላይ እንደካንሰር የተዛመተ ነው። የስርዓቱ አካሄድ ብዛትን ተከትሎ የጥራትን መንገድ በመሳቱ፤ በብርቱ ሲታመም እና ሲሰቃይ ቆይታል፡፡ ዛሬም የትምህርት ዘርፍ ከገባበት ጥልቅ የችግር ጉድጓድ፣ ከገጠመው ውስብስብ ችግር መውጣት አቅቶታል። ይሄንኑ ለመረዳት ደግሞ ብዙ ርቀትን መመለስ ሳይፈልግ የቅርቡን የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና አስደንጋጭ ውጤት ማስታወስ በቂ ነው፡፡

ለፈተናው ከተቀመጡት 980 ሺህ በላይ ተማሪዎች መካከል 30 ሺህ ብቻ ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ማግኘታቸው የሚታወስ ነው። ትምህርት ሚኒስቴር በብሔራዊው ፈተና በተደጋጋሚ የሚከሰተውን የፈተና ስርቆት እና ኩረጃን ለማስቀረት የተከተለው አሰራር ደግሞ ተሸፋፍኖ የሰነበተውን ሃቅ አደባባይ አውጥቶታል፡፡

በርግጥም በ12ኛ ክፍል ፈተና የተመዘገበው ውጤት እንደ አገር የቱ ጋር እንዳለን የሚጠቁም ነው። ለችግሩ ቀጣይ መፍትሄ ለማበጀት የሚያስችል እድል የፈጠረ ጭምር ነው። በተለይ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የማንቂያ ደውል እንደሚሆን ይታመናል።

ዶክተር እጓለ ገብረ ዮሐንስ ቀደም ሲል በጠቀስኩት መጻፋቸው፤ "ሰው ከሙሉ የሰውነት ደረጃ የሚደርሰው በትምህርት ነው፣ ይህንን ያልተረዳ ማኅበረሰብ ሆነ ሥርዓተ ትምህርት፣ በትምህርት የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣ መቸገሩ አይቀርም፤" ይላሉ፡፡

በዚህ ረገድ መንግስት ችግሩን የተረዳው ይመስላል። በሁሉም ደረጃ የትምህርት ስርዓቱን ስብራት ለመጠገን እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በተለይ በአገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ስርዓቱ ውድቀት ማሳያ በመሆን በሚጠቀሰው በከፍተኛ የትምህርት ላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ጥረት እየተደረገ ነው።

ከእነዚህ መካከል ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ይጠቀሳል። ትምህርት ሚኒስቴር ከአንድ ዓመት በፊት በ2015 ዓ.ም ጀምሮ የዩኒቨርሲቲ የመውጫ ፈተናው በሁሉም የመንግስትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ለመስጠት ወስኗል። ፈተናው በመጪው ሀምሌ ወር

> በዚህ ረገድ መንግስት ችግሩን የተረዳው ይመስላል። በሁሉም ደረጃ የትምህርት ስርዓቱን ስብራት ለመጠገን እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በተለይ በአገር አቀፍ ደረጃ የትምህርት ስርዓቱ ውድቀት ማሳያ በመሆን በሚጠቀሰው በከፍተኛ የትምህርት ላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ጥረት እየተደረገ ነው

በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች መሰጠቱ እርግጥ ሆኗል።

እንደ ማሌዢያ፣ ጃፓንና ቻይና የመሳሰሉ አገራት ያሉ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚገመግሙት በየዩኒቨርሲቲው የመውጫ ፈተና እየወሰዱ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ። እነዚህ አገራት ለፈተና ከተቀመጡ ተማሪዎች ምን ያህል እንዳለፉና እንደወደቁ በማየት የትምህርት ስርአታቸውን ይገመግማሉ። ይህም የትምህርት ስርአታቸውን ጉድለቶች ፈጥነው ለማየት እንደሚረዳቸው ይታመናል።

በኢትዮጵያ ውስጥም ይህ ዓይነት ልምድ ተጀምሮና ተጠናክሮ ቢቀጥል፤ የትምህርት ጥራቱ የተሻለ እንደሚያደርገው ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። በተለይ ከታችኛው ክፍል ጀምሮ በኩረጃ እየተፈተነ ላለው የትምህርት ስርአታችን አንድ እፎይታ ነው፤ ትውልዱ ራሱን እንዲፈትሽ፤ መጭው ትውልድም ትርጉም ላለው ትምህርት እራሱን እንዲያዘጋጅ ይረዳዋል። ይህን አይነቱ ተስፋ አዘል አዲስ አሰራር ሲመጣ ተግባራዊነቱን ከመደገፍ ባሻገር ለውጤታማነቱ አብሮ መሰለፍ ያስፈልጋል።

ከዚህ አንጻር ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎቻቸውን ለመውጫ ፈተናው ብቁ ለማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎች እና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች እየሰሩ መታየታቸው፤ አንዳንዶችም፤ ከዋና የመውጫ ፈተና (Exit Exam) ቀድመው የሞዴል ፈተና አዘጋጅተው እየሰጡ የሚገኙበት ሁኔታ የሚበረታታ እና እውቅና የሚሰጠው ነው።

ይህም ተማሪዎቻቸው ፈተናው አዲስ ከመሆኑ አንጻር፤ በፈተናው ዙሪያ በቂ ልምምድ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ የተሻለ የሥነ-ልቦናና የክህሎት ዝግጅት እንዲኖራቸው ያስችላል። የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ለመውጫ ፈተናው በስነ- ልቦናም በእውቀት እራሳቸውን የዓመታት ልፋታቸው ትርጉም እንዳያጣ መትጋት ይኖርባቸዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# የአፍሪካን ክብረወሰን የያዘችው አንገተ መለሉ ኢትዮጵያዊት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አብዛኞቻችን ውበት ምንድነው የሚል ጥያቄ ቢቀርብለን በአፍንጫ ሰልካካነት፣ በፀጉር እርዝመትና ዘንፋላነት፣ በቁመና እና በመሳሳሉት መገለጫዎች የራሳችንን አመለካከትና አተያይ ልናስቀምጥ እንችላለን። ይሁን እንጂ ውበት አንገተ መለሎነት (ረጅምነት) ነው ብንባል "እንዴት ሆኖ?" በማለት በግርምት ልንጠይቅም እንችላለን፡፡ ለዚህም ይመስላል "ውበት እንደተመልካቹ ነው" እየተባለ የሚተረተው፡፡

ዛሬ ላወጋችሁ ያሰበኩት ስለ አንገት ርዝመት ነው፡፡ ‹‹አንገተ ረጅም›› ስንል መቼው ቀድሞ ወደ አእምሮአችን በፍጥነት የሚመጣው ቃል ‹‹ቀጭኔ›› በመባል የምትታወቀው እንሰሳት ትመስለኛለች፡፡ ነገሩ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ ከሰው ልጆችም ቁጥራቸው ጥቂት ይሁን እንጂ በተፈጥሮ ረጅም አንገት የተቸራቸው ሰዎች መኖራቸው እንመለከታለን፡፡ በተለይ በተፈጥሮ በተቸሩት ረጅም አንገት ከሌሎች ሰዎች በተለየ መልኩ ማራኪና የሰውን ቀልብ የሚስቡ ቆነጃጅት ሞልተዋል፡፡

ረጅም አንገት ካላቸው የዓለም ሕዝቦች መካካል በማይናማርና በታይላንድ (Myanmar and Thailand) የሚገኙ ፓዳኡግ (Padaung) በመባል የሚታወቁ ጎሳዎች አንገተ ረጅም እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ከእነዚህ ጎሳዎች መካካል አንገተ ረጅም ተብላ የተመዘገበችው የአንዲት ሴት የአንገት ርዝመት 40 ሳንቲሜትር (15 inches) መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ወደ አፍሪካ ስንመጣ በቅርቡ አፍሪካውያን የድንቃ ድንቅ መዝገብ / ‹‹ Book of African Records››/ በመባል የሚታወቀው ድርጅት እንዳሳወቀው እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ በአንገተ ርዝመት ከአፍሪካ የመጀመሪያዋ ሪከርድ የያዘች ሴት በኢትዮጵያ መገኘቷን አሳውቋል። ከኢትዮጵያ የረጅም አንገት ባለቤት በመሆን እስካሁን ያለውን የአፍሪካን ክብረ ወሰን የያዘችው ኢትዮጵያዊት ሞዴል ሕይወት ባህሩ ትባላለች፡፡



ሞዴል ሕይወት ባህሩ

ሞዴል ሕይወት ባህሩ ተወልዳ ያደገችው ምዕራብ ሐረርጌ ገለምሶ በሚባል የምትታወቅ ቦታ ነው። እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስም ከእኩያቿ ጋር ወደ ትምህርት ቤት በመግባት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እዚያው ገለምሶ ተከታትላለች፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀችም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመከታታል ያስቻላት ዘንድ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የመጣችው ሞዴሊስቷ፣ አዲስ አበባ መምጣቷ ከትምህርቱ ጎን ለጎን የትወና ጥበባትንና የሞዴሊኒግ ትምህርት እንድትማር በር ከፍቶላታል፡፡

በሞዴል ትምህርት ላይ እያለች እስታር ሞዴል ኢን አፍሪካ (star model in Africa) በመባል በሞዴልነት እንደተመረጠች ትናገራለች፡፡ ሞዴል ሕይወት እንደምትለው፤ እስታር ሞዴል ኢን አፍሪካ በመባሏ በፋሽን እና ፎቶ ሞዴልነት ለመስራት እድሉን አግኝታለች፡፡ ይህንን እድልን በመጠቀም በጣሊያን፣ በፈረንሳይና በመሳሳሉ የተለያዩ ዓለም አገራት በመዞር የፋሽንና ፎቶ ሞዴሊንግ ሥራዎችን እየሰራች ትገኛለች።

‹‹እውነት ለመናገር እኔ ሞዴል እሆናለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር ›› የምትለው ሕይወት ሰዎች ሲያይዋት ሞዴሊንግ እንድትሞክር ቢገፋፏትም በትምህርት ላይ ስለነበረች ብዙ ትኩረት አልሰጠችውም ነበር፡፡ ትምህርቷን እንደጨረሰች በሰዎች ግፊት የሞዴሊንግ ሙያው ብትጀምር አሁን ላይ ስኬታማ መሆን እንደቻለች ትናገራለች፡፡

በዚህ መልኩ ‹ሀ› ብላ የጀመረችውን የሞዴሊኒግ ሥራዋን አጧጡፋ በቀጠለችበት ወቅት ከአፍሪካ አንገቷ ረጅም ሴት በመባል የአህጉሪቱን የድንቃ ድንቅ መዝገብ / ‹‹ Book of African Records››/ ላይ በመስፈር ሰርተፊኬት ማግኘቷን ትገልጻለች፡፡ የሞዴል ሕይወት ባህሩ የአንገት ርዝመት ፊት ለፊት 14 ሳንቲ ሜትር ሲሆን ከጎን ደግሞ 18 ሳንቲሜትር ርዝመት አለው፡፡

‹‹በቁመቴ ሁሉም ሰው ስለሚነግረኝ ሞዴል እንደምሆን እንዳሰበው አድርጎኛል፤ ነገር ግን የአንገቴ ርዝመት ግን የተለየ ነው ብዬ በፍጹም አስቤው አላውቅም ነበር›› የምትለው ሞዴሏ፤ በድንገት ጓደኞቿ በአፍሪካ ድንቃ ድንቅ መዝገብ ላይ እንድትመዘገብ እንዳነሳሷት ትገልጻለች፡፡ ‹‹በወቅቱ የአንገቴን ርዝመት በአፍሪካውያን የድንቃ ድንቅ መዝገብ እንዲመዘገብ በፎቶ ግራፍ ስልከው ፎቶዬን ያየው ሰው ማመን አልቻለም ነበር፤ በአካል ሲያየኝ ነው ያረጋገጠው›› ትላላች ሞዴል ሕይወት፡፡

‹‹ቀደም ሲል በኛ አገር እንደዚህ ለየት ያለ ተፈጥሮ ሆነ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መመዝገብ ነገር ብዙ አልተለመደም ነበር›› የምትለው ሕይወት፤ አሁን ላይ የተጀመረው የተለየ ተፈጥሮና ተሰጦ ያላቸው ሰዎች የማድነቁና የማበረታታት ሥራ ጥሩ ጅምር መኖሩን ትናገራለች፡፡

ሞዴሏ እንደምትለው፤ አሁን ላይ በሙያው የተለያዩ የዓለም አገራት በምትጓዝበት ጊዜ ኢትዮጵያ እያስተዋወቀች ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በቱሪዝሙ መስክ ሆነ በሌሎች ዘርፎች በርካታ የሚተዋወቁ ነገሮች ስላሉ ማስተዋወቁ ሥራ ትሰራለች፡፡ አሁን ላይ ደግሞ አንገቷ ረጅም በመባል የአፍሪካ ድንቃድንቅ መዝገብ / ‹‹ Book of African Records››/ ›› ያገኘችውን እውቅና በመጠቀም ከዚህ በበለጠ አገራን ለማስተዋወቅ ትጠቀምበታለች፡፡

‹‹እስካሁን ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ላይ የምትታወቀው በጦርነትና በረሃብ ነው›› የምትለው ሕይወት፤ በሞዴሊንግ ሙያ ዓለም ላይ በምትዞርበት ጊዜ ያጋጠማት ይሄው እንደነበር ገልጻለች፡፡ ይህንን አመለካከት በመቀየር የአገራችንን ገጽታ በመገንባት ረገድ ተባብረን ከሰራን አገራችንን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ እንችላለን ትላለች፡፡

ሞዴሏ እንደምትለው፤ ሴት መሆን በራሱ ፈተና አለው፡፡ ሴቶች ምንም አይነት ችሎታ ቢኖረን ‹አትችይም አታረጊውም› የምንባልበት ሁኔታዎች ይበዛሉ፡፡ ሴቶች ከሁሉ በፊት በራሳቸው ማመን አለባቸው፡፡ በራሳቸው አምነው እችላለሁ ብለው ከተነሱ ምንም ነገር የማድረግ አቅሙ እንዳላቸው መረዳት ይችላሉ፡፡ በተለይ ወጣት ሴቶች እንችላለን የሚለው አቅም ሰንቀው ሊነሱ ይገባል።

ሞዴሏ ‹‹እግዚአብሔር ሲፈጥርን ድንቅ አድርጎ የፈጠረን በመሆኑ በምን ነገር ማፈር የለብንም›› ትላለች። አንዱ ያለው ሌላው፤ ላይኖረው ይችላል፤ ይሄ የኔ ስጦታ ነው ብሎ ተቀብሎ ወደፊት በመውጣት ያለ ነገር ለዓለም ማስተዋወቅ ተገቢ ነው ብሏ እንደምታምንም ትናገራለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ባሉበት ለቆዩን ምስጋና !!!

**ግርማ መንግሥቱ**

ዛሬ ባለበት ነገ የሚገኝ ነገር ካለ እሱ ምን እንደ ሆነ ማወቅ ይከብዳል። እንደ ድሮው ጊዜ "ድንጋይ" አንዳንል እንኳን ድሮ የምናውቃቸው ድንጋዮች ዛሬ የሉም። ዛፎች እንዳንል አሁን የሚተከሉት እንጂ እድሜ ያስቆጠሩት ተመንጥረዋል፤ በአዲሱ አገላለፅ ተጨፍጭፈዋል። ወንዞች እንዳንል የደረቁትን ሳንጨምር ያሉትም ቀጥነዋል። ሀይቆች እንዳንል አብያታ እንኳን ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት ውስጥ ስንት ኪሎ ሜትር ነው ወደ ውስጥ ተሰብስቧል የሚባለው?። ስለዚህ ከሞባይል ካርዶች በስተቀር ባሉበት ሁኔታ ላይ ያሉ ነገሮች (ሸቀጦች፣ ምግቦች፣ ወንዝና ፏፏቴዎች፣ ጋራና ሸንተረሮች . . .) የሉም ማለት ይሆናልና አበስኩ ገበርኩ ያሰኛል። ኧረ እንደውም ያስፈራል (ፈሪሀ እግዚአብሔር ላለው)።

ነፍሱን ይማረውና የተረት ሰፈሩ (አይ ተረት ሰፈር፣ እንዴት ነሽ? ጋሽ ስብሀትና ሌሎችም ሰላም ብለውሻል፤ አልተገናኛችሁ ይሆን እንዴ?) ኮመዲያን ተስፋዬ ካሳ ለዓመት በአል ወደ አንድ በአካባቢው ወደ'ሚገኝ በግ ተራ ሄዶ "ይሄ ስንት ነው?" በማለቱ ምክንያት "347 ብር" የሚል መልስን በማግኘቱ ተደናግጦ "ምነው ዲፕሎም አለው እንዴ?" የሚል መልስ መልሶ መስጠቱን በዛው በተከበረ ሙያው አጫውቶን፣ አዝናንቶን፣ አስተምሮንና ተምብዮም ነበር። አይ ተስፍሽ ዛሬ ቢኖር ኖሮ ምን ይል ይሆን፣ ምንስ ብሎ ያጫውተን፣ ያዝናናን፣ ያስተምረንና ይተነብይ ይሆን ነበር።? ነው ወይስ ምንም ሳይል ደንግጦ በርሮ ይጠፋ ይሆን።?

ገዥ - ይሄ በግ ስንት ነው?

ሻጭ - 16ሺህ ብር።

ገዥ - መጨረሻው፤

ሻጭ - ይሄው ነው፤ አይቀንስም።

**እንደ እነ ዘይት፣ ስኳር፣ ማኪያቶ ምናምንቴዎች ኢሰብአዊ ተግባራት ውስጥ አልተዘፈቁም። ብታምኑም ባታምኑም አምስቱም ጨዋዎች ናቸው**

መግቢያ ቢበዛ ባህያ አይጫንም እንዲሉ (ባይሉም) መግቢያችንን ገታ አድርገን ወደ ጉዳያችን፣ ወደ ምስጋናችንና እጅ መንሳት ተግባራችን እንመለስ።

በእርግጥ ባለበት መቆየትን በተመለከተ ብዙ አይነት አተያዮች አሉ። ባለበት የቆየ ውሃ እንደሚበላው ሁሉ ባለበት የቆየ ጭንቅላትም ያው እንደሚታወቀው ነው። በመሆኑም ባሉበት መቆየት ወደ እነዚህ አካባቢ አይመከርም ማለት ነው።

ወደ ገበያና ግብይት፣ ገዥና ሻጭ ስንመጣ ግን ጉዳዩ ከእነዚህ የተለየ ሆኖ ነው የምናገኘው። ምክንያቱ ደግሞ በእነዚህ አካባቢ ባሉበት መቆየት ማለት ትርጉሙ የፖለቲካ መረጋጋት፣ የገንዘብ የመግዛት አቅም መጠናከር፣ የሸማቾች የመሸመት አቅም መኖር፣ የግሽበት መጠን መውረድ፣ ወዘተርፈ ሲሆን፤ ሲጠቃለል የሰው ልጅ በልቶ መኖር ማለት ስለሚሆን ነው።

እንደዚህ ጸሐፊ ግንዛቤና ተከታታይ እይታ እነዚህን ሁሉ በትክክል የተገነዘቡ ወገኖች ቢኖሩ አምስቱ የሞባይል ካርዶች (ከባለ 5 እስከ ባለ 100 ብር ያሉት) ብቻ ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ወገኖች ጎንበስ ብለን እጅ ልንነሳቸው ይገባል። እነሱም እንደ ሌሎች ሸቀጦች ከማበዳቸው በፊት ልንከባከባቸው፣ በሰላምታም ቢሆን ውለታቸውን ልንመልስላቸው ይገባል።

እስቲ ቆይ ትንሿ የፖስታ ሳጥን ቁጥር ከ85 ብር ተነስታ 600 ብር (ዓመታዊ የሳጥን ኪራይ) ስትገባ ባለ 5 ብሯ ካርድ 0.5 ሳ. እንኳን መጨመርን ማን ከለከላት፤ ህሊናዋ እንጂ ማንም።

እነ ምስር፣ ነጭ ሽንኩርት፣ እንቁላል . . . "አትንኩን"፣ "አትድረሱብን" እያሉ ደሀን ሲፀየፉ እነ ባለ 10 ብር ካርድ ከማን ያንሱና ነው ባሉበት ሁኔታ ላይ ሊገኙ የቻሉት፤ ሰብአዊነት ይዟቸው፣ ህሊናቸው ገዝቷቸው፤ ፈሪሀ እግዚአብሄር አድሮባቸው ነው እንጂ እነሱም ከማንም አያንሱም እኮ፤ ከማንም።

በስንዴ አገር ሞኮሮኒ ባለ 80 እና ባለ 90 (በኪሎ) ነኝ ሲል፣ ባለ 25 ብር ካርድ ብድግ ብሎ ከዛሬ ጀምሮ እኔም ባለ 100 ሆኛለሁ ቢል ማን ይከለክለዋል። የህሊና ጉዳይ፣ የሰብአዊነት ጉዳይ፣ የስነምግባር ጉዳይ . . . ነው እንጂ ዛሬ እኮ እሱም ከእህል እና ውሀ እኩል አስፈላጊ ሆኗል።

ዛሬ ቁርስ ለመብላት በክበባት ሳይቀር 100 ብር ዋጋ ሲያጣ፤ ዛሬ 100 ብር ሶስት ሲንግል እንኳን ለማስጎንጨት አይናፋር ሲሆን . . . እራሱ 100 ብር ለ200 ብር መልስ ሲሆን ባለ 100 ብሩ ካርድ እንጣጥ ብሎ ከዛሬ ጀምሮ እኔም ባለ 100 መሆኔ ቀርቶ ባለ1000 ሆኛለሁ ቢል አዳሜ ምን ታመጫለሽ፤ ምንም። እሱ ግን ጉዳዩ የህሊና ጉዳይ ነውና፣ ጉዳዩ የስነምግባር ጉዳይ ነውና፤ ጉዳዩ የአገርና የህዝብ ጉዳይ ነውና አላደረገውም። እሱ ብቻ አይደለም፤ በድምሩ "ካርድ" ወይም "የሞባይል ካርድ" ብለን በጥቅል የምንጠራቸው አምስቱም ካርዶች የነፃ ገበያ ጽንሰ-ሀሳብ እጅጉን የገባቸው፤ በተወዳድሮ ማሸነፍ እንጂ በአቋራጦ መክበር የማያምኑ በመሆናቸው እንደዚህ አይነት የስነምግባር ጥሰት ውስጥ አልገቡም። እንደ እነ ዘይት፣ ስኳር፣ ማኪያቶ ምናምንቴዎች ኢሰብአዊ ተግባራት ውስጥ አልተዘፈቁም። ብታምኑም ባታምኑም አምስቱም ጨዋዎች ናቸው። እነ ስነምግባር ለምኔ "አሳጣችሁን"፣ "አዋረዳችሁን"፣ "አሳቀላችሁን" . . . ቢሏቸውም፤ እነሱ ግን ማተባቸውን ለመበጠስ፣ ወገናቸውን ለማስለቀስ አልተዘጋጁም እና "ንክች ያባ ቢላዎ ልጅ" እንዳሉ ናቸው። እኛም ይህንን አቋማቸውን በመደገፍ ከጎናቸው ልንቆም ይገባን ነበር፤ አልነበረም?

ካርዶች፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ ". . . ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይቀይራልን?" የሚለውን በእናንተ፣ በሁላችሁም፤ ባምስታችሁም አየሁት። ስለ እውነት በእናንተ አየሁት፤ ኮራሁም። ወገን አለኝም አልኩ። የሌላውንማ . . . የለማ እውነት እሱ የለማ . . . (ገጣሚት ሜሮን ጌትነት ስፖርት ስታሰራ ነው ወይስ . . . - "ወደ ላይ" ስትል ነበር የተባለው?)።

በመጨረሻም፣ ርእሳችንን እንደግመዋለን። "ባላችሁበት ሁኔታ ላይ ያላችሁት የሞባይል ካርዶች፣ ቃላችሁን ያላዛነፋችሁት፣ ከነፈሰው ጋር ያልነፈሳችሁት፣ ከተስገበገበው ጋር ያልተስገበገባችሁት፣ "ሰው ተኮር" የሆናችሁት . . . አምስታችሁንም በድጋሚ እጅ እንነሳለን!!!"

# ነፃ ሃሳብ

# በክረምት፣ በአንድነት ወደ በጎነት

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

አሲዮ ብለን፣ የመስቀል ወፍና የአደይ አበባ፣ ቀጠሮ እንዳላቸው መስከረም ሲጠባ ስንል ገጥመን፣ በጥሌ ዜማ፣ በዘራቱ ጌታሁን እንቁጣጣሽ እንኳን መጣሽ፣ በአበቦች መሀል እንምነሽነሽ ብለን ተምነሽንሽንና የአዲስ ዓመት ብስራታችንን መስከረምን ሸኝተን፣ ከገናና ከፋሲካ፣ ከአረፋና ከረመዳን በረከት ተቋድሰን፣ በኑሮ ውድነትና በኮሮና ስጋት ተይዘን፣ በጦርነትና በሞት ስጋት ተከበን እየተንገዳገደን እንሆ ሰኔ ላይ ከተምን፡፡

ጊዜ ህይወት ነው..ጊዜ ስኬት ነው፡፡ ጊዜ ለራሳችንም ሆነ ለአገራችን በጎውን እንድናደርግ እድል የሚሰጠን አጋጣሚ ነው፡፡ እነሆ በዚህ የጊዜ ምህዋር ላይ ተረማምደን የክረምት ሁሉ አባት በሆነው ሰኔ ላይ ቆመን ክረምትን ለበጎነት በሚል እሳቤ እራሳችንን እያዘጋጀን ነው፡፡ እርግጥ የዘንድሮው ክረምት የተፈጥሮን ህግ የሻረ በሚመስል ሁኔታ በኢትዮጵያ ታሪክ ዓመቱን ሙሉ ከበጋ የተኳረፍንበት ጊዜ ነበር ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

በትላንት፣ ዛሬ እና ነገ ምልልስ ውስጥ ዘመን ይሄዳል ዘመን ይመጣል፡፡ በዚህ ሁሉ የጊዜ ሂደት ውስጥ ክረምትን ታከው የሚመጡ በጎ እና እኩይ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ እንደባህሪው ክረምት ነፍራቃ ነው፡፡ ምድርን በጥቁር ጉም ሸፍኖ፣ በነጎድጓድና በመብረቅ ታጅቦ ነፍስን የሚያስጨንቅ የወቅቶች ነጭናጫ ነው፡፡

ጊዜ ህዝብ ለአገር፣ አገር ለትውልድ የምትሰጠው የቅብብሎሽ በትር ነው፡ በጊዜአችን ውስጥ በጎ ነገር ስናጣ፣ ጊዜአችንን ተጠቅመን ለራሳችንም ሆነ ለሌላው መልካም ነገር ማድረግ ሲያቅተን ያኔ ዘመን የሸመነው ሰውነታችን እያረጀና እየጃጀ እንደ ልብስ እናልቃለን፡፡ ከዛም ከእድሜ አመሻሽ ላይ ቆመን ‹ወይኔ እንዲህ አድርጌ ቢሆን ኖሮ› ብለን እንቆጫለን፡፡ ከዚህ መቆጨት በኋላ ራሳችንን የምናጽናናበትትን እውነት ፍለጋ ብዙ እንተከዛለን፡፡

ሰኔ የክረምት መግቢያ በር ነው፡፡ ክረምት በሰኔ በር ገብቶ ነው እስከ አዲስ ዓመትና ከዛ በኋላ እስካለው ጊዜ የሚዘልቀው፡፡ በእኚህ በተለመዱ የክረምት ወራት ውስጥ ቤት የሌለው ብቻ አይደለም ቤት ያለው ሳይቀር በክረምት ለበቅ ይሸነቆጣል፡፡ እናም ያን ሽንቆጣ ከራሳችንም ሆነ ከወገናችን ላይ ለማንሳት ክረምትን ታከው ለሚመጡ ስቃዮች በጎ ስራን በመስራት ተገን መሆን ይቻላል፡፡

ሰኔ ዝርክርክ ብሎ የሚያዝረከርከን የጿጋና የመከራ ጌጣችን ነው፡፡ ወፍራም በመልበስና የላመ በመብላት አንሸሽውም ምክንያቱም ወፍራም መልበስ የማይችሉና የላመ ለመብላት አቅም የሌላቸው ወገኖች አሉንና ነው፡፡ ሰውነት ስለ ሌላው መታመም ነው፡፡ ሰውነት በሌሎች ስቃይ መሰቃየት ነው፡፡ ክረምት ደግሞ ስለሌላው እንድንታመምና እንድንሰቃይ የሚያደርግ ጥሩ አጋጣሚያችን ነው፡፡

ምክንያቱም በክረምት ቤት የሌላቸው፣ በክረምት መሸሸጊያ ያጡ ነፍሶች ብዙ ናቸውና ነው፡፡ ምንያቱም በክረምት ቤታቸው ዝናብ የሚያስገባ፣ በድህነት መውደቂያ ያጡ አሉና ነው፡፡ ክረምት ለሰው ልጅ እንባና ሳቅ ነው፡፡ የሞቀ ቤት ያለን እኔና እናንተ እንደምንስቅ ሁሉ ክረምት በመጣ ቁጥር የሚያለቅሱ፣ መግቢያ የሚያጡ ነፍሶች ጥቂቶች አይደሉም፡፡

ክረምት ለአገራችን በጎውን እንድንሰራ እድል ከሚሰጡን አጋጣሚዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ለበጎ ተግባር ጥሩ አጋጣሚም ይመስለኛል፡፡ በእርግጥ ለበጎ ተግባር ሆነ ለአገር መልካም ለማድረግ ሁሉም ጊዜአቶች እኩል ቢሆኑም የክረምትን ያክል አገር ወገን የሚረዳበት ጊዜ አለ ብዬ አላስብም፡፡

ምክንያቱ ደግሞ ክረምት ሲመጣ ይዟቸው የሚመጣው ብዙ ችግሮች ስላሉ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ጎርፍ፣ የአካባቢ መጥለቅለቅ፣ የመንገድ መበላሸት፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በቂና አስተማማኝ መኖሪያ ስለሌላቸው በክረምቱ መቸገር የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። እንግዲህ ክረምትን ለበጎነት የሚለው መነሻ ሃሳቤ ትርጉም የሚያገኘው እዚህ ጋ ነው፡፡

እንደሚታወቀው አገራችን ብዙ ድሆች የሚኖሩባት አገር ናት፡፡ የእኛን እርዳታ፣ የእኛን ድጋፍ የሚፈልጉ አያሌ የማህበረሰብ ክፍሎች እዛም እዚም አሉ፡፡ ክረምት ሲሆን ደግሞ ይሄ ማህበራዊ ምስቅልቅል እጅጉን ይጨምራል፡፡ በዚህም መሰረት ለወገናችን የምንደርስለት እና አለኝታነታችንን የምናሳይበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን፡፡

በጎ መሆን ከኪሳችን የምናወጣው ሳይሆን ከልባችን የምናወጣ ነገር ነው፡፡ በዙሪያችን የእኛን በጎ መሆን የሚሹ ብዙ ማህበራዊ ችግሮች አሉ፡፡ አገር የምትቆመው የአንዱን ችግር አንዱ የኔ ነው ብሎ ሲነሳ ነው፡፡ ዜግነት ትርጉም የሚያገኘው የወገኖቻችንን ስቃይ መሰቃየት ስንችል ነው፡፡ ለራስ ብቻ በማሰብ ውስጥ፣ ለራስ ብቻ በመኖር ውስጥ ዜግነት የለም፡፡

አገር ማለት ምንድነው ብሎ ለጠየቀ የመልካም ልቦች ህብረት ነው የሚል መልስ ያገኛል፡፡ በእውቀታችን፣ በጉልበታችን፣ በገንዘባችን ለአገርና ወገን አለኝታ መሆን ካልቻልን እኛ ምንም ነን ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ክረምት ይዞብን የሚመጣው ማህበራዊ ቀውስ የታወቀ ነውና ከወዲሁ መረዳዳታችንን ማጠንከር ይኖርብናል፡፡

ክረምት በመጣ ቁጥር የምንሰማቸው በርካታ ሞቶችና የንብረት ውድመቶች አሉ፡፡ ወቅቱን ባልጠበቀው በዘንድሮው ክረምትም ተመሳሳይ ነገር ተስተውሏል፡፡ የባሰው ክረምት ሰኔን ታኮ የሚመጣው ከፊታችን ያለው ወራት በመሆኑ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ መሰል ችግሮችን እንዳናስተናግድ እድል ይፈጥርልናል፡፡

> **ከዚህ መቆጨት በኋላ ራሳችንን የምናጽናናበትን እውነት ፍለጋ ብዙ እንተከዛለን፡፡ ሰኔ የክረምት መግቢያ በር ነው። ክረምት በሰኔ በር ገብቶ ነው እስከ አዲስ ዓመትና ከዛ በኋላ እስካለው ጊዜ የሚዘልቀው፡፡ በእኚህ በተለመዱ የክረምት ወራት ውስጥ ቤት የሌለው ብቻ አይደለም ቤት ያለው ሳይቀር በክረምት ለበቅ ይሸነቆጣል**

በጎ መሆን የሰውልጅ ሁሉ ባህሪ ነው፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ በጎነትን በሚመለከት ብዙ እየሱሳዊ መልዕክቶች ተጠቅሰው እናገኛለን፡፡ በኤፌሶን መልዕክት ላይ እንዲህ የሚል መልዕክት አለ ‹በጎውን ስራ እንድንሰራ በክርስቶስ እየሱስ ተፈጠርን› የሚል፡፡ መቼም የትም የሰው ልጅ ለሌላው እንዲኖር ነው የተፈጠረው፡፡

በጎነታችንም በዙሪያችን ካሉ የሚጀምር ነው፡፡ በጎነታችን ከሰፈርና ከጎረቤት የሚጀምር ነው፡፡ ክረምቱ ስቃይ እንዳይሆንባቸው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ወገኖቻችንን ችግሮቻቸውን ጠይቆ በመረዳት መፍትሄ መስጠት ሰኔን የምንበቀልበት አንዱ መንገድ ነው፡፡

ቤት ለሌላቸው ቤት በመስራት፣ ቤታቸው ያረጀባቸውን ቤታቸውን በማደስ፣ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ወገኖቻችንን ክረምቱን የሚያልፉበትን መንገድ በመፍጠር ክረምቱን በበጎ ስራ ማሳለፍ እንችላለን፡፡ ክረምት ከመቼውም ጊዜ በላይ በተለይ በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነው፡፡

በዛው ልክ ከተጠቀምንበት ክረምት ጸጋችን ነው። የሚያዘንብልንን ዝናብ ለበጎ ነገር የመጠቀም አቅሙና ህብረቱ ካለን ከነበርንበት የድህነት ዝቅታ ከፍ ማለት ይቻለናል፡፡ በዓለም ላይ ቀዳሚ ያደረገንን የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራም ያሳካነው እኮ በክረምት ጸጋ ነው፡፡

ከራሳችን አልፈን አፍሪካን ያማከለ የአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴ ያደረግነው እና እያደረግን ያለነው እኮ በሰኔ ጉርምርምታ ታጅበን ነው፡፡ የታላቁን ህዳሴ የውሀ ሙሌቶች ያስተናገድነው እኮ በክረምት ኃይል ነው። እጆቻችንን ለልማት፣ ልቦቻችንን ለመልካም ስራ ያተጋነው እኮ ክረምት ስለመጣ ነው፡፡ ዘንድሮም ብዙ ችግኞችን ለመትከል እቅድ ይዘን እየተንቀሳቀስን ያለነው እኮ በክረምት ጸጋ ነው፡፡

እንደዚሁም ደግሞ የአቅመ ደካሞችን ቤት አድሰን ለመመረቅና ለመመስገን የተነሳነው እኮ በዚህ ጊዜ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ የመኖር ዋስትናችን የሆነው የአርሶ አደሩ መሬት የተሻለ ምርት ይይዝ ዘንድ ክረምት እጅግ አስፈላጊያችን ነው፡፡ አብቅለን ለመብላትና እያሰቃየን ካለው የኑሮ ውድነት ተላቀን ጥሩ ኑሮ ለመኖር ክረምት ዋስትናችን ነው፡፡

ከዚህ በተለየ ደግሞ አዲሱን ዓመት በደስታና በፍቅር እንድንኖር ክረምት ያሻናል እንዴት ላለኝ እንዲህ እለዋለው..ሁሉም አዲስ ዓመት የሀምሌና የነሀሴን ክረምት ጠጥተው ያማሩና የቆነጁ ናቸው፡፡ የምንናፍቀው መስከረም እንኳን አምሮና ተውቦ የምናገኘው ከፊቱ ባሉት የክረምት ወራት ተደግፎ ነው፡፡

ዓለም ላይ መለያችን የሆነው፣ ጿጉሜን ተንተርሶ ነፍስ የሚዘራው አደይ አበባ እኮ የሀምሌና የነሀሴ ጽንስ ነው። በዓመት አንድ ጊዜ ብቅ ብላ የምትሰወረው የመስቀል ወፍ እኮ ጎጆዋን የምትቀልሰው በመስከረም ተስፋ ነው.. ተስፋዋን የሰጣት ደግሞ ክረምት ነው፡፡ እናም ክረምት ከተጠቀምንበት ጸጋችን ነው ካልተጠቀምንበት ደግሞ መከራችን ይሆናል፡፡

ከእኛ የሚጠበቀው በክረምት ጸጋ እየተጠቀምን ችግሩን በጋራ ማሸነፍ ነው፡፡ ክረምት የፍቅር ወቅት ነው። ከመቸውም ጊዜ በላይ በዚህ ወቅት መዋደድና መፋቀር ይኖርብናል፡፡ በክረምት ጠብና ቁርሾ የማይታሰብ ነው። በክረምት ሁሉም ጦረኞች ጦር የሚጥሉበት፣ ይቅር ለእግዜር ተባብለው ወደ ስራ የሚገቡበት ጊዜ ነው፡፡

በክረምት እልሀኞች እልሃቸውን ትተው ወደ ልማት የሚሰማሩበት ነው፡፡ ምክንያቱም የክረምት ጸጋ በዓመት አንዴ ስለሆነ ነው፡፡ ቤታችንን በጋራ ሰርተን፣ ፍቅራችንን በጋራ አለምልመን ቀጣዩን የበጋ ወራት በደስታና በአንድነት እናልፍ ዘንድ ዛሬን መረዳዳት ግድ ይለናል፡፡ መንግስት ይሄን የክረምት ወቅት ለብዙ የልማት ስራዎች መጠቀም አለበት፡፡ እኛም ዜጎች በዚህ ክረምት ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች በጎ ስራ በመስራት ኃላፊነታችንን መወጣት ይጠበቅብናል፡፡

ክረምትን በጦርነት ያሳለፈ ማህበረሰብ ቀጣዩ ጊዜው የስቃይ ጊዜ ነው የሚሆነው፡፡ በክረምት ያላበቀለ፣ በክረምት ይቅር ያልተባባለ ጠበኛ መጪው ጊዜ ጥሩ አይሆንም፡፡ በክረምት ቂማችንን ካልተውን፣ በክረምት ሞፈር ካልጨበጥን መጪው ጊዜ ይበረታብናል፡፡ እናም ክረምትን ለይቅርታና ለልማት፣ ለመረዳዳትና ለመተጋገዝ እናውለው፡፡

አገር መውደድ ሰውን መውደድ ነው፡፡ የአገር ፍቅር ስሜት ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ አስቸጋሪ ጊዜዎችን በጋራ ማለፍ ነው፡፡ ከፊታችን ያሉ ጊዜዎች መልካም የሚሆኑት ዛሬ ላይ በምናደርገው ድርጊት ነውና ከነውር ወጥተን ሊጠቅመን በሚችል በጎ ስራ ላይ ማሳለፍ ችግሮቻችንን የምናሸንፍበት መንገድ ነው፡፡

ልባችንን ለበጎ ምግባር ካስገዛን ክረምት አስቆን የማያልፍበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ ክረምት መከራ የሚሆነው የሌላውን ጩኸት ላለመስማት ጆሯችንን ስንደፍን ነው፡፡ ከፍ ብዬ እንዳልኳችሁ ከመቸውም ጊዜ በላይ ክረምት ስቃይ የሚሆንባቸው ብዙ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ፡፡ ከመከራው አንጻር ጭራሽ ክረምት ባልመጣ ብለው የሚመኙ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

ይሄ ደግሞ ክረምት ምን ያክል ችግረኛው ማህበረሰብ ላይ እንደሚበረታ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ለወገናችን ልንደርስለት የሚገባው፡፡ በእንዲህ ያለው ወቅት ነው አጋርነታችንን ልናሳይ የሚገባን፡፡ በክረምት የሚያለቅሱ አይኖች፣ የሚባቡ ልቦች ጥቂት አይደሉም፡፡ ዙሪያችንን ቃኘት ማድረግ ብንችል ብዙ ችግረኛ ሰዎችን ማግኘት እንችላለን፡፡

በክረምት ቤታቸው ዝናብ እያስገባ የሚሰቃዩ እናቶች ጥቂት አይደሉም የነሱን እንባ ማበስ ደስታው ምን ያክል እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡ በክረምት መጠጊያ አጥተው ጎዳና ላይ እትት የሚሉ ችግረኛ ወገኖች አሉ እነሱን መታደግ በረከቱ ምን ያክል እንደሆነ አይጠፋንም።

በክረምት መንገዶች በጎርፍ ይጥለቀለቃሉ፣ ይቦረቦራሉ፣ ጉምና ጭጋግ ስለሚበዛ በዚህም የትራፊክ አደጋ ከፍ ይላል፡፡ እኚህ ሁሉ ክረምት ወለድ አገራዊና ማህበራዊ ችግሮቻችን እልባት የሚያገኙት በእኛ መልካም ተግባር ነውና ትብብራችን እንዳለፈው ጊዜ አደጋዎች እንዳይፈጠሩ ቅድመ ዝግጅት ስለሆነ ልንበረታ ይገባል፡፡

በክረምት የመሬት መንሸራተት አደጋ ያይላል፡፡ በከተማም ሆነ በገጠር እንዲህ አይነቱ አደጋ የተለመደ ነው፡፡ ይሄን አይነቱን አደጋ ለመቅረፍ ከአሁኑ የእርከን ስራዎች ቢሰሩ መልካም ይሆናል፡፡ አምና በዚህ ሰዐት የክረምትን መግባት ተከትሎ የተከሰቱ በርካታ የተፈጥሮ አደጋዎች አሉ፡፡

እነዛን አደጋዎች ለመከላከል ሁላችንም ባለንበት ማህበራዊ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ግድ ይላል፡፡ ክረምትና የትራፊክ አደጋም እንደዚሁ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነው ከትላንት ዛሬ የዘለቁ ናቸው፡፡ የመሬት መንሸራተት ስለሚኖር በዛው ልክ የትራፊክ አደጋው ይጨምራል፡፡

ጉሙና ጭጋጉ ሲጨመርበት ደግሞ ወትሮ ሀይ ባይ ያላገኘው የትራፊክ ችግራችን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖ ለከፋ አደጋ ተጋላጭ ነው የሚያደርገን፡፡ እግረኛም ሆነ አሽከርካሪ መጪውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ከወዲሁ ለራሱ ዋስትና ቢሰጥ እንደአገር የሚደርስብንን ክስረት መቀነስ እንችላለን፡፡

በሁሉም ነገር ለአገራችን ዘብ የምንቆምበት ጊዜ ላይ ነን፡፡ በልማቱም በሰላሙም በእርቁም ለአገራችን ውለታ የምንውልበት ሰሞን ላይ ነን፡፡ ብልህ ሰው ነገውን ዛሬ የሚሰራ ነው፡፡ ብልህ ሰው አስቸጋሪ ጊዜዎችን በመተባበር የሚያልፍ ነው፡፡ እኛም በቀና ልብ በበጎ ስራ ነጋችንን ዛሬ ማነጽ ይቻለናል፡፡ እንዲህ አይነቱ የመተባበር መንፈስ በግለኝነት የደበዘዘችውን ኢትዮጵያ የሚያነጻ ነው፡፡

አስቸጋሪ ጊዜዎች ለብቻ የሚታለፉ አይደሉም። በተለይ አሁን ያለንበት ጊዜ ከመቼውም ጊዜ በላይ አንድነታችንን የሚፈልግ ነው፡፡ መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆን በመልካም ልብ የምናከናውናቸው ተግባራት ብዙ ናቸው፡፡ ከወዲሁ ተጋግዘን እልባት ካልሰጠናቸው በቀር ክረምትን ተከትለው የሚመጡ ማህበራዊ ቀውሶች ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡

ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሀኒቱ እንደሚባለው ክረምት ወለድም ሆኑ በጋ ወለድ ችግሮቻችን በአንድነት ከተነሳንባቸው የሚረቱ ናቸው፡፡ አገር በመረዳዳት ውስጥ ውብ ናት፡፡ ለብቻ ቆመን፣ ለብቻ አስበን የምናሳካው አንዳች ነገር የለም፡፡ የኔ ችግር የማህበረሰቡ ችግር ነው። የአንተ ችግር የኔና የሌላው ሰው ችግር ነው፡፡ እናም በአንድነት ወደበጎነት..

ኢኮኖሚ

ግብርና

# ለአረንጓዴ አሻራ መርሃግብሩ ዘላቂነት

ስምስም መንግሥቱ

የሁለተኛው ዙር አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ዘንድሮም በህዝብ የንቅናቄ ተሳትፎ ሊከናወን «ነገን ዛሬ እንትከል» በሚል መሪ ሀሳብ ሰሞኑን በይፋ ተጀምሯል። በዚህ በዘንድሮው አምስተኛው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊየን የዛፍ ችግኞች ለመትከል ዝግጅት ተደርጓል።

በመጀመሪያው ዙር ለተከታታይ አራት ዓመታት የተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር በከፍተኛ የህዝብ ንቅናቄ ተከናውኗል፡፡ በመርሀ ግብሩ 20 ቢሊየን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ 25 ቢሊየን ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በመርሀ ግብሩ 20 ሚሊየን የሚገመት ህዝብ እንደተሳተፈበትም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሩ የዛፍ ችግኝ ተከላ በተጠናከረ የህዝብ ተሳትፎ እየተካሄደ ይገኛል። የችግኝ ተከላው በህዝብ ንቅናቄ እየተካሄደ ያለበትን መንገድ አስመልክቶም የተለያዩ ሙያዊ ሀሳቦች እየተንጸባረቁም ይገኛሉ፡፡ አንደኛው ወገን የችግኝ ተከላው በህዝብ የንቅናቄ ተሳትፎ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት የሚል ሲሆን፣ ሌላው ወገን ደግሞ ዘመቻው ዘላቂነት እንዲኖረው ለማስቻል በተደራጀ የተቋም አሰራር መመራት አለበት የሚል ሀሳብ በማንሳት ይሞግታል፡፡

የኢትዮጵያ ደን ልማት ዋና ዳይሬክተር አቶ ከበደ ይማም የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃግብሩ በህዝብ የንቅናቄ ተሳትፎ መቀጠል እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡ አቶ ከበደ መርሃግብሩ የዜጎች መሆኑን በመግለጽ፣ አካባቢን የመንከባከብና የመጠበቅ ኃላፊነትም የትውልዱ፣ አልፎም የዜጎች ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ላይ የመንግሥት ኃላፊነት ልማቱ በቴክኖሎጂ እንዲከናወን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ ባለሙያዎችን በማቅረብ እገዛ ማድረግ፣ የገንዘብ ድጋፍ በሚያስፈልግበት ወቅትም በማቅረብ ድጋፍና ክትትሉን ማጠናከር ነው ይላሉ፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብሩ በዚህ መልኩ መከናወኑ አግባብነት አለው ብለው የሚገልጹት አቶ ከበደ፣ የዛፍ ችግኝ ተከላ ሥራ ከፍተኛ መዋእለነዋይ ይጠይቃል፤ በአገር አቅም ደግሞ የሚቻል አይደለም፤ ይህንን መወጣት የሚቻለው በመተጋገዝ ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ በደን መመናመንና በአፈር መሸርሸር በመሬት መራቆት ኢትዮጵያ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባታል፡፡ ይህንንም ችግር በርብርብ ካልሆነ ሥራውን ለአንድ አካል ብቻ በመተው ውጤታማ መሆን አይቻልም። ለአንድ ወገን የሚተው ሥራ ችግሩን ያባብሰዋል እንጂ አይቀረፍም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ህብረተሰቡ እያደረገ ያለው የጉልበት አስተዋጽኦ በገንዘብ ቢተመን ብዙ ቢሊየን ብር ይገመታል፡፡

ህብረተሰቡ የሚያደርገው ተሳትፎ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ወጭ እንደሚያስቀርም ነው የሚናገሩት። በመሬት አቀማመጥ አስቸጋሪነትና በመሬት መራቆት ከፍተኛ ተግዳሮት የገጠማቸው እንደነ ኮሪያና ቻይና ያሉ አገሮች ችግሩን መቋቋም የቻሉት በዜጎች ተሳትፎ እንደሆነም አቶ ከበደ አብነት ጠቅሰው ያብራራሉ። የችግኝ ተከላ ስራው በዘመቻ መካሄድ የለበትም የሚሉ ወገኖች ጉዳዩን ከተለያየ አቅጣጫ ካለማየት፣ ያለውን ተግዳሮትና ዜጎችም ኃላፊነት እንዳለባቸው ካለማጤን የሚሰጡት ሀሳብ አድርገው ይወስዳሉ፡፡

«ነገን ዛሬ እንትከል» በሚል መሪ ቃል የተጀመረው ሁለተኛው ዙር የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃግብርም ለም የሆነች ኢትዮጵያን ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ የዜጎች ኃላፊነት መሆኑን የሚያጠናክር መሆኑን ነው አቶ ከበደ ያመለከቱት። አሁን ላይ ያለውም ሆነ ተተኪው ትውልድ የሚጠቀመው ዛሬ በተሰራው ሥራ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትም አንጻር፤ አንድ ችግኝ ፀድቆ ለምርት እስኪደርስ ረጅም ዓመት የሚወስድባቸው አንዳንድ የዓለም አገራት መኖራቸውን አቶ ከበደ ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ ግን ለእጽዋት መጽደቅ ምቹ የሆነ የአየርፀባይ እንዳላት ይናገራሉ፡፡ ይህም ችግኙ ረጅም ዓመት ሳይወስድበት ለምርት እንዲደርስ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፣ ምርቱን ለተለያየ የኢንዱስትሪ ግብአት ማዋል የሚቻልበት ዕድል መኖሩን አስረድተዋል። ከዛፍ ችግኝ ተከላው ጎን ለጎን በሚከናወነው የተለያየ ፍራፍሬ ልማትም እንዲሁ ምርት በአጭር ጊዜ ውስጥ ደርሶ ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት እድል መኖሩን ገልጸዋል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ሀብት ማፍሪያና መበልፀጊያ እንደሆነ ሁሉም ዜጋ ተገንዝቦ የየድርሻውን መወጣት አለበት በሚል ሀሳብ በዛፍ ችግኝ ተከላው ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲጠናከር መደረጉን ያስረዳሉ፡፡

በማህበረሰብ ንቅናቄ የሚከናወነው የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃግብር ዘላቂነት፣ ችግኙን በእንክብካቤ እስከ መጨረሻው ውጤት ካለማድረስ እንዲሁም ከባለቤትነት ጋር ተያይዞ ለሚነሳው ሀሳብም አቶ ከበደ፤ አስተያየቱ ግምት እንጂ በጥናት የተደገፈ እንዳልሆነ ነው የሚገልጹት። የተተከሉትን ችግኞች መንግሥት ብቻ እንዲንከባከባቸው መጠበቅ የለበትም ይላሉ፡፡

አቶ ከበደ ክፍተቶች ያሏቸውንም አንስተዋል፡፡ በወል መሬት ላይ እንክብካቤ ማድረግ ላይ ጉድለት መኖሩን ጠቅሰው፣ ይህም ቢሆን እንደትልቅ ችግር መታየት እንደሌለበት ነው የሚናገሩት፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት እንዲሁም የሚያስፈልጋቸውን የሙያ ድጋፍ እና ቴክኖሎጂ ለይቶ በማሟላት ክፍተቱን ማረም እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡

ህብረተሰቡ በወል መሬት ላይ የጋራ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለው የምስክር ወረቀት የሚያገኝበት አሰራር በመኖሩ ሁሉም ባለቤት እንዳለው ያስረዳሉ። ከዚህ አንጻር በጋራ ለመጠቀም በሥራው ላይም በጋራ መሳተፍና መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ በእስካሁኑ ተሞክሮም የተተከሉ ችግኞችን ተንከባክበው ለውጤት ያደረሱ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦችና ተቋማት መኖራቸውንም ነው የገለጹት፡፡

በህዝብ ንቅናቄ ዘመቻ እየተከናወነ ያለው የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃግብር ዘላቂነት እንዲኖረው በተቋማዊ አደረጃጀት መመራት አለበት ሲሉ የቀድሞው በአረንጓዴ ልማት ኢንስቲትዩት የአፍሪካ የደንና የተፈጥሮ መፍትሄዎች አስተባባሪ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙት ዶክተር ገመዶ ዳሌ «አረንጓዴ አሻራ መርሃግብር በዘመቻ መጀመሩ አገራዊ መነቃቃትን ፈጥሯል፡፡ ለውጡም ቀላል ተደርጎ አይወሰድም» ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የቀድሞው የኢትዮጵያ ብዝሐ ህይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም የቀድሞው የአካባቢ ጥበቃና ደን ልማት ሚኒስትር ሆነው ያገለገሉት ዶክተር ገመዶ፤ የዛፍ ችግኝ መትከል አስፈላጊነት ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ የባህሪ ለውጥ ማምጣት መቻሉ ትልቅ እመርታ እንደሆነም ነው የተናገሩት፡፡

በዚህ ረገድ የተሰራው ሥራ ትልቅ ሀብት ነው ብዬ እወስዳለሁ ያሉት ዶክተር ገመዶ፣ ነገር ግን ማነቃቃት ለምን ተፈለገ? ዘመቻውስ ለምን? በዚህ ሁሉ ጥረት ምንድነው ማግኘት የተፈለገው? የሚለው መፈተሽ እንዳለበት ይናገራሉ፡፡

በሁሉም አቅጣጫ ርብርብ ሲደረግ የነበረው የተተከለው የዛፍ ችግኝ መጠን እና የህዝብ ተሳትፎ ብዛት ላይ መሆኑን ጠቅሰው፣ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ህዝብን በንቅናቄና በዘመቻ የማሳተፉና የማነቃቃቱ ተግባር መቀጠል ይኖርበታል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

መሠረታዊ ትኩረት መሆን ያለበት በተቋማዊ አደረጃጀት እንዲመራ ማድረግ ላይ ሊሆን እንደሚገባም ነው ያስገነዘቡት፡፡ ዘመቻውንና ተቋማዊ ሥራው ተቀናጅቶ መተግበር ይኖርበታል። ከፍተኛ መዋእለነዋይ ፈሰበት ለተከላ የሚዘጋጀው ችግኝ በአግባቡ ስለመተከሉ የሚጠይቅ፣ ድጋፍ ሲያስፈልግና የክትትል ሥራም ለመሥራት አቅዶ የሚተገብር ተቋም ያስፈልጋል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እንደ ዶክተር ገመዶ ገለጻ፤ በተቀናጀ ሁኔታ የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀት ይኑር ሲባል ለችግኝ ተከላ ሥራ ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። አጠቃላይ የደንና የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣ በሀብት አጠባበቅና አጠቃቀም ላይ ግንዛቤው ያደገ ማህበረሰብ ለመፍጠር መሆን አለበት። በተቀናጀ መልኩ መመራቱ ተሳታፊነቱም ዘላቂነት እንዲኖረው ለማስቻል ያግዛል።

እንዲህ ያለው አሰራር ሲጠናከር በጊዜያዊ ኩነቶች ላይ የሚደረግ ተሳትፎን ያስቀራል። ለእዚህም በተለይ ማህበረሰብ ላይ የማያቋርጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሰራት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድም መገናኛ ብዙሃንን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ተቋማዊ አደረጃጀቱ በበጀት እንዲከናወን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የወል መሬትን ጨምሮ እየተከናወነ ያለው የዛፍ ችግኝ ተከላ ባለቤት አለው ሲሉ አቶ ከበደ የሰጡን ሀሳብ ዶክተር ገመዶ አይስማሙበትም፡፡ ዶክተር ገመዶ በወል መሬት ላይ እየተካሄደ ባለው የችግኝ ተከላ ላይ ክፍተት እንዳለ ይገልጻሉ፡፡ በወል መሬት ላይ እንዲተከል የሚፈለገውን ያህል ችግኝ እንዲተከል ድጋፍ የሚያደርግ አካል ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ዶክተር ገመዶ እንዳሉት፤ የዛፍ ችግኝ ተከላው የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ ካለው ጠቀሜታ ባሻገር ለማህበረሰቡ የኢኮኖሚ ምንጭ መሆን ይኖርበታል። ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የዛፍ ዝርያዎች እንዲተክሉም ሆነ ወደፊት እንዴት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው በሚለው ላይ ለመስራት በባለሙያ እገዛ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በተቋማዊ አደረጃጀት ነው፡፡

የተፈጥሮ ሀብትን የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም ሊኖር እንደሚገባና እንደአገርም መታየት እንዳለበት ዶክተር ገመዶ ይጠቁማሉ፡፡ ከሌሎች አገሮች ተሞክሮም የዛምቢያን ለአብነት እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ። በዛምቢያ የአረንጓዴ ልማትና ዘላቂ እድገት፣ የደን ልማት፣ የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር መሥሪያቤቶች እንደሚገኙ ጠቅሰው፣ በዚህ ደረጃ የተቋቋመ ተቋም የሌላት ኢትዮጵያ ብቻ እንደሆነች ይገልጻሉ፡፡ ኢትዮጵያ የአካባቢ ደን የአየርንብረት ሚኒስቴር ቢኖራትም በመዋቅር መፍረሱን አስታውሰው፣ ተቋማዊ አደረጃጀትን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ ለሁሉም ነገር መሠረት መሆኑ ግንዛቤ ተይዞ አሰራሩ ጭምር መስተካከል እንዳለበትም ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

በሁለተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃግብር የአየር ንብረት ለውጥ ፈተናዎችን የሚቋቋሙ አገር በቀል ችግኞች እንደሚገኙበት ባለፈው ሐሙስ በአፋር ክልል ተገኝተው መርሃግብሩን ያስጀመሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገልፀዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር አረንጓዴ አሻራ ለትውልድ የሚተረፍ ቅርስ እንደሆነ፣ የአየር ንብረት ለውጥንና የአካባቢ መራቆትን ለመቋቋም እንደአገር የተወጠነ አገርበቀል አካሄዳችን ነው ሲሉ ገልጸዋል። ለምግብ የሚውሉ እጽዋትን መትከል የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበት አንዱ መንገድ እንደሆነም ተናግረው፣ መርሃግብሩ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በሚከናወነው የችግኝ ተከላም እንደ አፕል፣ መንደሪንና ሌሎች ፍራፍሬዎች ያሉትን ማስፋፋት ይገባልም ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በሁለተኛው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ዜጎች በኃላፊነት ስሜት እንዲሳተፉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡ የመጀመሪያውን ዙር ጨምሮ በአጠቃላይ በሚከናወነው አረንጓዴ አሻራ መርሃግብር 50 ቢሊየን የዛፍ ችግኞችን ማልማት ከተቻለ እንደአገር ትልቅ እመርታ እንደሚመዘገብና አሻራ ማሳረፍ እንደሚቻልም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡



በመርሀ ግብሩ ባለፉት አራት አመታት 25 ቢሊየን ችግኞችን መትከል ተችሏል

ማህበራዊ

# አስኳላ





ፎቶ ኢዮብ ተፈሪ

አገር ተረካቢ ትውልድ እያፈሩ የሚገኙ መምህራን ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፣

# ከመማር ማስተማር ባለፈ - ቅን ትውልድ የማፍራት ዘመቻ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር የስነ ዜጋና ስነምግባር ትምህርት ለማስተማሪያነት ባቀረበው መፅሐፍ ምዕራፍ አራት ላይ እንዳስቀመጠው፤ ሥነምግባር ማለት፡- በምንኖርበት ማኅበረሰብና አካባቢ ተቀባይነትን ያገኘ መልካም ባሕርይን መላበስና መተግበር ማለት ነው።

ሥነምግባራችን ከአስተዳደጋችን፣ አኗኗራችንና ሥነልቦናችን ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። ሥነምግባር ፍላጎታችንና ምርጫችን፣ በጎና ጸያፍ ሥራዎቻችን የሚመነጩበት የማንነት መገለጫ ነው።

የሰው ልጅ በተፈጥሮው እንደሚኖረው አስተዳደግ ማኅበራዊ ገጠመኝ፣ መልካም ወይም መጥፎ ሥነምግባርን ሊላበስ ይችላል። የሰው ልጅ በልጅነት ዘመኑ መልካም የሚባሉ ዓለማዊና መንፈሳዊ ሥነምግባሮችን እንዲያውቅና እንዲተገብር በሚያበረታታ ቤተሰብና ማኅበረሰብ ውስጥ ካደገ ሐቅንና መልካም ነገርን የመውደድና መጥፎ ነገርን የመጥላት ባሕርይን ያዳብራል። መልካም ባሕርይ አንድን ሰው በጎ ተግባራትን ያለማንም አስገዳጅነት እንዲያከናውን ያደርጋል።

እንዲህ ዓይነት ባሕርይ የተላበሰ ሰው የመልካም ሥነምግባር ባለቤት ነው ሊባል ይችላል። ሥነምግባር ከሰው የሚመነጭና ካለማንም አስገዳጅነት የሚፈፀሙ ተግባራት መገለጫ ነው። ለምሳሌ ሆደ ሰፊነትና እርጋታ፣ ታጋሽነትና ቻይነት፣ ቸርነትና ጀግንነት፣ ፍትሐዊነትና በጎነት፣ ወዘተ፣ የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው።

በተቃራኒው የሰው ልጅ የባሕርይ ማስተካከያ አሊያም የቤተሰብ ክትትል ካልተደረገለት፣ ወይም በመጥፎ አስተዳደግ ካደገ፣ መጥፎውን መልካም፣ ቆንጆውን ደግሞ የሚያስጠላ አድርጎ የመመልከት ባሕርይ ሊኖረው ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሰው አስነዋሪ ተግባራትን ያለምንም እፍረት ይተገብራል፤ ይናገራል። አንድ ሰው፣ አንድን መጥፎ ሥራ በንግግርም ሆነ በተግባር ያለምንም እፍረት የሚናገርና የሚተገብር ከሆነ፣ መጥፎ ሥነምግባርን የተላበሰ ነው እንለዋለን።

ከመጥፎ ሥነምግባር መገለጫዎች ውስጥ ተንኮል፣ ሐሰት መናገር፣ ግልፍተኝነት፣ ስግብግብነት፣ እብሪተኝነት፣ ተሳዳቢነት፣ ወዘተ፣ ይገኙበታል። የሥነምግባር መርሆዎች በጋራ የሚኖሩ ወይም የሚሠሩ ህዝቦች፣ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች በጋራ የሚመሩበት የሚከተሉትና የሚተዳደሩበት ራሳቸውንና ሥራቸውን ለመቆጣጠር የሚያግዙ የሥነምግባር መመሪያዎች ናቸው።

የሥነምግባር መርሆዎች እንደ አገሩ፣ እንደ ባህሉ፣ እንደ ሙያው ወዘተ.. ሊለያዩ ይችላሉ። ሆኖም በብዙ ሕዝቦች፣ ባህሎችና ሙያዎች ተቀባይነት አላቸው፡፡

መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ ለአገር እድገት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ዛሬ የአገራችንን እድገት ወደ ኋላ እየጎተቱ ላሉ እንደ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት እንዲሁም በስልጣን መመካት ዋነኛ መንስኤ የሥነምግባር ጉድለት ነው። ለማኅበራዊ ሕይወት ጠንቅ የሆኑ እንደ ሌብነት፣ ሱሰኝነት፣ አጭበርባሪነት፣ ስግብግብነት፣ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት ወዘተ የመብዛታቸው ምስጢርም የሥነምግባር ጉድለት ነው፡፡

ስለዚህ መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ ማፍራት ለጤናማ ማኅበራዊ ሕይወትና ለአገር ብልጽግና ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ መልካም ዜጋ መሆን የሚፈልግ ሰው የማኅበረሰቡንና የሙያውን የሥነምግባር መርሆዎች አውቆ ማክበርና መተግበር ይጠበቅበታል። ይህንን ከሚያስፈጽሙና የዕውቀት ምንጭ ከሆኑት መካከል ደግሞ ትምህርት ቤቶች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡

በአባባል ደረጃ እንደሚገለጸው፤ እውነተኛ ትምህርት «ልብንና አዕምሮን ያርቃል»፡፡ ለዚህም ትምህርት ቤቶች በስነምግባርና ስነዜጋ ትምህርታቸው ከእውቀት ባሻገር ያለውን እውነታ ለትውልዱ ያሳዩበታል፡፡ ምክንያቱም ስነምግባር እውቀት ብቻ ሳይሆን ኑሮም ነው፡፡

በስርዓተ ትምህርት ተካቶ በመምህራን ብቻ የሚሰጥ የነበረ የአቅም ማጎልበቻ አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቃል፡፡ ውልደቱ አካባቢ መድረሻው ደግሞ ስኬት ነው። ብልሃት፣ እውነት፣ እውቀትና ልቀትን የምናገኝበት አገራዊ ልምድና ጥበብ ነው፡፡ ስነምግባር የነገዋን አገር የምናይበት መነጽርም ነው፡፡

በፉክክሩ ውስጥ ጥበብን የምናገኝበት ኃይል፡፡ ጥበብ ደግሞ አስተዋይነት፤ ከእኔነት ይልቅ ለሌሎች መትረፍ፤ የእኛነት ባህል ነው፡፡ እናም እንደ አገር የተያዘውም አቅጣጫ ይህንን በመመርኮዝ መሥራት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ እውቀትና እውነታዎችን በትምህርት ለማገናኘት መሞከር ሲሆን፤ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ የስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት ተብሎ በአንድነት ይሰጥ የነበረውን ለየብቻ በማድረግ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡

የዜግነት ትምህርት ለብቻው የስነምግባር ትምህርት ላይ ያተኮረውን ደግሞ ግብረገብ በሚል እንዲሰጥ ሆኗል። መማር ሽምደዳና ለቁጥር ከፍታ ከሆነ ከምረቃ በኋላ ነገሮች ያከትማሉ፡፡ ከሰዎች ጋር በትብብር ለመስራት፣ ሰርቶ ለመደሰትና የፈለጉት ስኬት ላይ ለመድረስም አያስችልም፡፡

መማር ከስርዓት መያዝና ግብረገብ ከመሆን ጋር ተያይዞ እንዲቀጥል ለማስቻል ከታችኛው ክፍል ጀምሮ ተግባሩ እንዲከወን እድሎች ተመቻችተዋል፡፡ በእርግጥ ሰሚ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ወጥተው የተማሩትን ልምድ እንዲያደርጉ ማበረታታትም ይገባል፡፡ በተጨማሪም ወላጅና የአካባቢው ሰው ነባር ባህሉንና ወጉን እያሳወቃቸው በመልካም ስነምግባር እንደያድጉ ማገዝም ይኖርበታል፡፡

ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ ተቋማትና ድርጅቶችም እንዲሁ ተግባሩን ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክያቱም ዜጋን በመልካም ምግባር ማነጽ ለአንድ አካል የሚተው አይደለም፡፡ ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ተቋማት በዚህ ተግባር ላይ ተሰማርተው የድርሻቸውን ሲወጡ የምንመለከተው፡፡

ድርጅቱ ቅን ኢትዮጵያ ይባላል፡፡ ቅንነትን፣ መተባበርንና መከባበርን እንዲሁም መደናነቅን ባህል ያደረጉ ዜጎችን መፍጠር ዋነኛ አላማው ነው፡፡ እናም ይህ ድርጅት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን አገር አቀፋዊ የማመስገንና የመደናነቅ ቀንን በየዓመቱ እያከናወነ ይገኛል፡፡ ቀኑን ዘንድሮ ለሦስተኛ ጊዜ "ተማሪ ለአገር ሰላም" በሚል መሪ ሀሳብ አክብረውታል፡፡

**ዛሬ ላይ መምህራን መልካም ዘር እየዘሩ ይገኛሉ። ድንግል መሬት ላይ የተዘራ ዘር ደግሞ ፍሬው ውጤታማ እንደሚሆን አያጠራጥርም**

በዓመታዊው አገር አቀፍ የመመሰጋገንና የመደናነቅ ቀን ላይ የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ ባደረጉት ንግግር፡- ትናንት የነበረንን መልካምነትና አመስጋኝነት ባህል እያጣን በመምጣታችን አንድ ከሚያደርጉን እልፍ እሴቶች ይልቅ ልዩነታችን ላይ በማተኮራችን ለተለያዩ ችግሮች ተዳርገናል። ስለሆነም እንደ አገር ቅንነት፣ መልካምነትና አመስጋኝነትን ባህሉ ያደረገ ተተኪ ትውልድ ማፍራት ላይ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ለአንድ አካል የምንተወው ሳይሆን ሁሉም ተረባርቦ የሚያመጣው ነው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን የመደናነቅና የመመሰጋገን ባህላችን ከፍ ያለ ነበር ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ አገራዊ ጀግኖቻችንን ዓለም እንዲያውቃቸው ሆኗል። ይህ መልካም እሴት እንዲጠናከር በትኩረት መሥራት ግን በብዙ መልኩ ይቀረናል። እናም ልዩ ትኩረታችን ሆኖ ልንሰራበት ይገባል፡፡ በዚህ ደግሞ የቅን ኢትዮጵያ ማህበር ያሳየው ቁርጠኝነት የሚመሰገን ነው ብለዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር ከመደበኛ መማር ማስተማር ሥራው በተጨማሪ አገር ተረካቢው ትውልድ በሥነምግባር የታነጸና መከባበርና መመሰጋገንን እሴቱ ያደረገ ሆኖ እንዲቀረጽ የግብረ ገብ ትምህርትን የመደበኛ ትምህርቱ አንድ አካል አድርጎ እየሠራ ይገኛል፡፡ ሆኖም ሁሉም ባለድርሻ አካላት አመስጋኝነትን፣ መደናነቅንና ቅንነትን እሴት ያደረገ ተተኪ ትውልድ ለማፍራት በትኩረት መሥራት ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም አሁን ላይ የአብሮነታችን ቱባ የተተረተረው ከሚያቀራርቡን በርካታ እሴቶች ይልቅ ጥቃቅን ልዩነታችን ላይ በማተኮራችን ነው፡፡ እናም አሁን የደበዘዘውን መልካም እሴት መልሰን የምናጠናክርበትና ቅንነት፣ መመሰጋገንና የመደናነቅ ባህላችንን የምናሳድግበት ጊዜ ነውና እድሉን መጠቀም ያስፈልገናል፡፡ ለዚህ ደግሞ ይህንን መልካም እሴት ባህሉ ያደረገ ዜጋ ማፍራት ላይ ግድ መስራት አለብን፡፡

ዶክተር ፋንታ እንደገለጹት፤ በቅርቡ ዜጎች ትምህርት ቤታቸውን በተለየ መልኩ የሚያግዙበት ሕጻናትም ከማመስገን ባለፈ የሚያስመሰግን ተግባር ምን እንደሚመስል የሚማሩበት መርሐ ግብር ይፋ ይደረጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መላው ኢትዮጵያውያን በቅንነት ከሚኒስቴሩ ጎን በመቆም የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል በሚደረገው አገራዊ ንቅናቄ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የቅን ኢትዮጵያ ማኅበር ቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ካሣሁን አበሩ በበኩላቸው፤ እየደበዘዘ የመጣውን የአመስጋኝነት ባሕል ለመመለስ ከአገር ተረካቢ ልጆች መጀመር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከትምህርት ቤቶች እንዲጀመር ተደርጓል። ለዚህ ደግሞ ከቤተሰብ ቀጥሎ ልጆችን ኮትኩቶ በማሳደግ አገር ተረካቢ ትውልድ እያፈሩ የሚገኙ መምህራን ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል። ምክንያቱም ነገ መልካም እሴት የተላበሱ ዜጎች እንዲኖሩ እየሰሩ ነውና፡፡ ዛሬ ላይ መምህራን መልካም ዘር እየዘሩ ይገኛሉ፡፡ ድንግል መሬት ላይ የተዘራ ዘር ደግሞ ፍሬው ውጤታማ እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡

የቅን ኢትዮጵያ መሥራችና የሀሳቡ ባለቤት ዶክተር ቶሎሳ ጉዲናም የሚሉት ሕጻንነት የነገ አገር ተረካቢ ዜጎች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እነዚህ ሕጻናት ከመለያየትና ዘረኝነት ርቀው የአመስጋኝነት፣ የመደናነቅና ቅንነትን መልካም እሴቶችን ተላብሰው እንዲያድጉ መረባረብ አለባቸው፡፡

የሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ አገራዊ አንድነት ለማጠናከርና ዜጎችን በሙሉ የሚያሳትፍ እንዲሆን መከባበርና መደናነቅ ሁነኛ መፍትሄ ነው፡፡ መመሰጋገን፣ መከባበርና መተባበር አንድነታችንን ይበልጥ ያጠናክራል። በዚህም ኢትዮጵያውያን ጠንካራ የመመሰጋገን ባህል ያላቸው ህዝቦች መሆናቸውን ለትውልዱ ማስተማርና እንዲኖረው አርአያ እየሆኑ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆንላቸው ደግሞ ለተደረገላቸው ብቻ ሳይሆን ለሚደረግላቸው ጭምር አመስጋኝ ይሆናሉ፡፡

ምስጋና የመከባበርና መተባበር መገለጫ ነው። መደናነቅና መከባበር እንዲሁም አመስጋኝ መሆን አንድነትን አጠናክሮ ትልቅ የመስራት ኃይልን ያጎናጽፋል። ለነገሮች ልዩ ትኩረት መስጠት፤ መተባበርና ከሌሎች ጋር አብሮ መሥራት ይዳብራል፡፡ ለአገሩ ብሎ የሚሰራ ትውልድን ያበዛል፡፡ ተስፋን ስንቅ አድርገው ገና ከጅምሩ ጎበዝ ተማሪ እንዲሆኑም ያግዛል፡፡

ኢትዮጵያ የገጠሟትን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎች ተቋቁማ በአሸናፊነት እንድትቀጥልም ያስችላል፡፡ ስለሆነም እጅ ለእጅ ስንያያዝ ኢትዮጵያዊነት ውበታችን ይጎላልና ራሳችንን አድምቀን ለዓለም ጭምር ብርሃን እንሁን እንላለን፡፡ ሰላም!!

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ በብዝሃ ሕይወት ሀብቶቻቸው የበለጸጉ ከተባሉ 25 አገራት መካከል አንዷ ናት››

*ዶክተር ገመዶ ዳሌ*
*በኢንስቲትዩቱ የአፍሪካ የደንና የተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝ መሪ*

**አስቴር ኤልያስ**

ዶክተር ገመዶ ዳሌ ተቀማጭነታቸው በኮትዲቯር አቢጃን ሲሆን፣ በዓለም አቀፉ የአረንጓዴ እድገት ኢንስቲትዩት ውስጥ የአፍሪካ የደንና የተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝ መሪ ሆነው ካለፈው ጥር ወር ጀምሮ በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በባዮሎጂ፤ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በጀርመን አገር በኢኮሎጂ ሰርተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችንም ሲያስተምሩም ቆይተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት የተቋሙ ስራ አስኪያጅ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፣ የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴርን ደግሞ በሚኒስትርነት መርተዋል፡፡ ከሚኒስትርነት ከተነሱ በኋላ ለሁለት ዓመት ያህል በዓለም አቀፉ የአረንጓዴ እድገት ኢንስቲትዩት የኢትዮጵያ ቢሮ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ኢንስቲትዩት የመንግስታቱ ድርጅት ሲሆን፣ በአባልነት የያዘውም 45 አገራትን ነው፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ መስራች ከሚባሉት አስር አገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ ተቋሙ የተቋቋመው በ2012 ሲሆን፣ ሐሳቡን ያቀረቡትም ሆነ በወጪም በኩል ድጋፍ ያደረጉት የወቅቱ የደቡብ ኮሪያ መሪ ነበሩ፡፡ ጉዳዩን አስመልክቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሮ የተከፈተው በዚያው ዓመት ነው፡፡ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ከመደገፍ እስከ ትግበራው ኢትዮጵያ በቁርጠኝነት የተቀበለችው ከመሆኑም ሌላ በሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ እንዲካተት እስከማድረግ ድረስም ሁኔታውን ስታስኬደው ነበር፡፡ የዛሬው ወቅታዊ ከዚሁ ከአረንጓዴ አሻራና ከብዝሃ ሕይወት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ አዲስ ዘመንም በዘርፉ የካበተ ልምድ ካላቸው ከዶክተር ገመዶ ዳሌ ጋር ቃለ ምልልስ አድርጎ ተከታዩን አጠናቅሯል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዘርፉ ያልዎ ልምድ የካበተ ነውና ተፈጥሮ ሀብትን በመንከባከብ የሚገኘውን ፋይዳ በተመለከተ ካለዎት አተያይ ጥያቄያችንን ብንጀምር?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ ያለብን ለምንድን ነው የሚለውን ስንመልስ በዚህ ውስጥ የአገር በቀል ዝርያዎች ጉዳይ ይመጣል፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን የምንጠብቀው ለሰው ልጅ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መንፈሳዊ ብሎም ባህላዊ አገልግሎቶች ሁሉ ከተፈጥሮ ሀብት ስለሚገኙ ነው፡፡

አንድ ሰው ጤናማ እንዲሆን ከተፈለገ ከተፈጥሮ ሀብት ጋር መታረቅ አለበት፡፡ ምክንያቱም የአዕምሮም ጤና ጭምር በተፈጥሮ ሀብት ይታከማል፡፡ ሁሉም ምግቦቻችንን ብንወስድ ሁሉም ማለት በሚያስደፍር መልኩ በተፈጥሮ ሀብት የመጡ የብዝሃ ሕይወት ሀብቶቻን ውጤቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጤፍን ብንወስድ የኢትዮጵያ የብዝሃ ሕይወት ሀብት ነው፡፡

አገር በቀል ዝሪያዎችን መጠበቁ ግድ የሚለን ውሃን፣ ንጹህ አየርን፣ የዳበረ አፈርን እንዲሁም ምግብንም ጭምር ለማግኘት ነው፡፡ እዚህ አገር በቀል በራሳቸው የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብር ውስጥ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ በመሆናቸው የውጪውን አምጥተን ከምናስገባ የመጀመሪያ መስተጋብር ጤነኛ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረጉ የተፈለገውን አገልግሎት ማግኘት ያስችለናል፡፡ ለዚህም ነው የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ ቦታቸው መገኘት አለባቸው የምንለው፡፡

ይህን ስንል ግን በዓላማ፣ ለተለየ የኢኮኖሚ ፍላጎት፣ ለተለየ የኢንዱስትሪ ፍላጎት የውጪዎቹን ችግኞች አንጠቀምም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ባህር ዛፍን ብንወስድ የቀደሙ መሪዎቻችን ባህር ዛፍን ወደኢትዮጵያ እንዲገቡ አድርገው ባይተከል ኖሮ እንጦጦ ዛሬ ባዶ ሆኖ አዲስ አበባ ከተማ በኅርፍ መጥለቅለቅ በቸገረው ነበር። ለዚህም ነው በዓላማ ተክለን የምንጠቀምበት ከሆነ አገር በቀል ብቻ መሆን አለበት ተብሎ አይደመደምም፡፡ በመሆኑም እንደየሁኔታው የሚወሰን ይሆናል፡፡

እስካሁን ከተሰሩት ውስጥ ለአብነት ያህል የወዳጅነት አደባባይን ብንወስድ በዚህ የወዳጅነት አደባባይ ላይ የተሰራውን ስራ ሲጤን ችግራችን የቦታ ጥበት ሳይሆን የአስተሳሰብ ጉዳይ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በከተማ ውስጥም እንደ ወዳጅነት አደባባይ አይነት ግቢ ሰርቶ ማሳየት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ገጠር ሲሆን ሁሉም ነገር ለእርሻ፣ ከተማ ሲሆን ሁሉም ነገር ለግንባታ ከማድረግ የተመጣጠነ ተፈጥሮ እና ልማትን ያገናዘበ ተግባር ታቅዶ መከናወን እንዳለበት አንድ ማሳያ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ግን በተወሰነ ጊዜ በዘመቻ አይነት ሳይሆን በስርዓት መመራት አለበት፡፡

ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት እያለን አገር በቀል ዝሪያዎች እየጠፉ ስለሆነ ለተፈጥሮ ሀብት መጥፋት ግንባር ቀደም ጠር ወይም ጠላት ግብርና ነው እንል ነበር። ይህን ነገር በአንድ ወቅት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩም ባሉበት በተቻለኝ አቅም ለማስረዳት ሞክሬ ነበር፡፡

አሁንም ግልጽ ለማድረግ ግብርናን የእኛ አመራር የተረዳበት ቅኝት ትክክል ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ እርግጥ ነው ግብርና አብዛኛውን ሕዝባችንን የሚመግብ ነው፡፡ ከስራ አንግለልም ሲታይ ብዙውንም ሕዝብ ቀጥሮ የያዘ ዘርፍ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ዘርፍ ስለመሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ግብራችን ግን አሁን ያለውን ፍላጎት አርክቶን ለቀጣዩም የአገር ምጣኔ እድገት ለማረጋገጥ ከተፈለገ ሁሉንም አጥፍቶ ግብርናን በማድረግ ሳይሆን ለግብርና ራሱ መሰረት የሆነውን መሰረት ላይ አተኩሮ መስራት ግድ ይላል፡፡

ለምሳሌ በአሁን ወቅት የማዳበሪያ ግዥ በጣም ጨምሯል፡፡ የመሬታችንን ለምነት በአግባቡ መንከባከብ ሲገባን በማዳበሪያ ኃይል ምርት እንዲሰጠን እያደረግን ነው፡፡ ይህ መሬታችንን ጭምር የሚበክል ነው፡፡ ግብርና ያለ ተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ማስኬድ ከባድ ነው፡፡ ለምሳሌ አሜሪካ በግብርና ዙሪያ ከፍ ያለ ምርት አምራች አገር ናት፡፡ ለአብነት በኦቶዋንና በሚሺጋን አካባቢ ያለው የመሬት አቀመጣጥ ሲታይ ለጥ ያለ ነው፡፡ ስፍራውም ሲታይ የግብርና ማሳው ደን እንጂ የግብርና ውጤት አይመስልም፡፡ በማሳው ዙሪያ የሚታየው ደን ነው፡፡ ያደጉ አገሮች የሚያርጉት እንዲህ ነው፡፡

ወደእኛ አገር ሲመጣ ዛፍና ግብርና ጠላት ይመስል ደኑ ሁሉ ይጠፋና ማሳው ባዶውን እንዲቀር ይደረጋል፡፡ ዝርያዎች የተሻለ ምርት ለመስጠት ምቹት የሚሰማቸው አካባቢው ቀዝቀዝ ያለውን ነው፡፡ አብዛኛው የግብርና ምርቶቻችንን የምናገኘው የወንዴውና የሴቷ አካል በተለያየ ቦታ ላይ ሆነው ነው፡፡ እነዚህ አካላት ምርት እንዲሰጡን ከተፈለገ መዳቀል አለባቸው፡፡ ያንን የማዳቀል አገልግሎትን የሚሰጡት ቢራቢሮ፣ ንብ እና ሌሎች ነፍሳት ናቸው፤ እነዚህ ነፍሳት ደግሞ ላገለገሉን አገልግሎት በደረሰኝ ጠይቀውን ቢሆን ክፍያቸው ከባድ ይሆንብን ነበር፡፡ እኛ እያደረግን ያለው ጸረ አረም መድሃኒትም ሆነ ሌላው ሌላው በመርጨት እነዚህ ነፍሳት ተግባራቸውን እንዳያከናውኑ እንቅፋት እንፈጥርባቸዋለን፡፡ ስለሆነም የአዳቃይ ነፍሳትን ጤናማነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ የግብርና ቦታዎች ዛፎችን መትከል ይበጃል፡፡ ከዚህ አኳያ አሁን የተጀማመሩ ነገሮች አሉ። ስለዚህ አንዱ ዘንድ የሚሰራው ተፈጥሮ ሀብት በብዙ መልኩ ለግብርና ምርትና ምርታማነት ላቅ ያለ ፋይዳ አለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በአረንጓዴ አሻራ እየተከናወነ ያለው ተግባር ለዚህ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው ማለት አይቻልም? አሰራሩንስ እንደምን አዩት?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** በአሁኑ ወቅት ያለው አመራር እያከናወነ ያለው ተግባር ለሪከርድ ያለመ የችግኝ ተከላ በመርህ ደረጃ እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ጉድለቶች አሉበት ወይ? ከተባለ አዎ ጉድለቶች አሉበት፡፡ ይህ ስራ በራሱ በተቋም ደረጃ እየተመራ ነው ቢባል መልሴ አይደለም ነው። በዚህ ሁሉ ውስጥ ሆኖ ግን እየተሰራ ያለውና የተወሰደው እርምጃ ‹‹ይቻላል›› የሚለውን በሚገባ ያመላከተ ነው፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁርጠኝነት ሌሎቹን ሚኒስትሮች እንዴት እንዳንቀሳቀሰ ማጤን ተችሎበታልና በጥሩ ሁኔታ ቀጥሏል የሚል አተያይ አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት በተለይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፤ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ የልማት ስትራቴጂን ከመተግበር አኳያስ ያበረከተችወን እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** በዚህ ስራ ግልጽ አቋም አለኝ፡ ፡ ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ የልማት ስትራቴጂን የዓለም ማኅበረሰብ ገና በጉዳዩ ላይ የጋራ መረዳት ሳይኖራቸው ያንን ማድረግ ይቻላል ብላ ብቻ ሳይሆን የስትራቴጂዋ አካል አድርጋ የገለጸች አገር ናት፡፡ ይህም የሆነው እኤአ 2011 ላይ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአገሪቷ መሪ ለኢትዮጵያ የሚያዋጣት የተለመደው መንገድ ሳይሆን የአረንጓዴ እድገት አማራጭ ነው በሚል በመንቀሳቀሳችንን ነው ዓለም የሚያውቀን፡፡ ከዚያ በኋላ ስትራቴጂው የአገሪቱ ሰነድ ሆኖ ከጸደቀ በኋላ ወደአተገባበር ስንመጣ ደግሞ የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሲታቀድ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት የእቅዱ አካል ሆኖ ነው የታቀደው፡፡

ከዚያ በመቀጠል ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በወሰዱት እርምጃ ያንን በተሻለ መልክ በተግባር ለመግለጽ ችለዋል፡፡ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ እና ኃይለማርያም የየራሳቸውን ጥረት አድርገዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ የዶክተር ዐቢይን ለየት የሚያደርገው ግን ስራውን ራሱ የእርሳቸው ስራ አድርገው እያስኬዱት መሆኑ ነው፡፡ እርሳቸው የስራው ባለቤት በመሆን መስራታቸው ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ግን በአሁኑ ወቅት እየተሰራ ያለው ስራ በእጅጉ የሚያስመሰግንና ውጤቱም ያማረ መሆኑን ሳልናገር ማለፍ አልፈልግም፡፡ ለምሳሌ አስቀድሜ እንደጠቀስኩት በወዳጅነት ፓርክ የተያዘው የተፈጥሮ ሀብት ሲታይ የሚያስመሰግን ነው፡፡ በዚህ መልክ የተሰሩ በርካታ ስራዎች በመሆናቸው ለዓለም ማኅብረሰብ በአግባቡ የተገለጹ አይመስለኝም፡፡


ፎቶ -አዩብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- ሰኔ 1 ቀን 2015 ዓ.ም በይፋ መተከል የጀመረው ሁለተኛ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አለ፤ በመጀመሪያው ዙር በተካሄደው መርሃግብር ምን የተገኘ ስኬት አለ ይላሉ? ከዚህስ በኋላ ምን መደረግ አለበት?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** የአንደኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ በጣም በተሳካ ሁኔታ የማኅበረሰብ ንቅናቄ ተፈጥሮ ተሰርቷል፡፡ ይህ ንቅናቄ በሌሎች አገሮች አይገኝም፡፡ አጋጣሚ ሆኖ አሁን ከምሰራበት ከኮትዲቯር አቢጃን ወደ ዛምቢያም እና ዑጋንዳ በስራ ምክንያት በሔድኩበት ወቅት ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር ሁለቱም ዘንድ ያለው አሰራር ከእኛ ጋር የሚመሳሰል አይደለም፡፡ እኛ ዘንድ ልዩ የሚያደርገው የተፈጠረው ንቅናቄና ይህ ንቅናቄ ደግሞ የተመራበት አግባብ ጥሩ ነው፡፡ ይህ የተፈጠረው የሕዝብ ንቅናቄ መቀጠል አለበት ባይ ነኝ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ሁሉም አመራር ፕሮግራሙን የራሱ እንዲያደርግ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዚህ በኋላ ፕሮግራም በራሳችሁ ስሩ ቢሉ ስንቱ ሚኒስትር፤ ስንቱ የክልል መሪና ሌላውም ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ጉዳዩን ሊያስኬደው ይችላል? ቢባል በአግባቡ ስለመሰራቱ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ይህ ሊጤን የሚገባው ነው፡፡

ሶስተኛው ደግሞ ጥሩነቱ በርካታ ችግኞች መተከላቸው ነው፤ እዚህ ላይ መተኮር ያለበት ጉዳይ ግን በጣም ብዙ ችግኝ የተተከለው የት ነው? የተተከሉትስ ለምን ዓላማ ነው? የሚለውን ነገር የምናጠራበት ታማኝ የመረጃ ስርዓት የለንም፡፡ ሲጀመር እየተከልን ያለነው አገር በቀል ዝርያዎችን ነው የሚባል ከሆነ ሐሳቡ ጉድጓዱ ከመቆፈሩ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ወቅታዊ

## «ኢትዮጵያ በብዝሃ ሕይወት ሀብቶቻቸው የበለጸጉ ...»

**ከገጽ 10 የዞረ**

በፊት አገር በቀል ዝርያዎችን ከዘር ለቀማው ጀምሮ ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

ለምሳሌ አገር በቀል ዝርያ ለአዲስ አበባ እና ለሞጆ ተመሳሳይ መሆን የለትም፡፡ ስለዚህ የትኞቹ ዝርያዎች የት? እና ለምን? ዓላማ መተከል አለባቸው? የሚለው ነገር እየተሰራ ያለው መጤን አለበት፡፡ በእኔ አተያይ እንዲህ አይነቱ ክፍተት በሁለተኛው ዙር ላይ ይስተካከላል ብዬ አምናለሁ፡፡ ከዘር መስብሰብ እስከ ችግኝ ማፍላትና ቦታ መርጦ መትከል ድረስ ጥንቃቄ ይደረጋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በዚህ መልኩ ሰርተን ኢትዮጵያውያን ችግኝ ተክለው የጠፋውን የደን ሽፋን በዚህ ያህል መጠን አሳደጉ፤ ሕዝባቸውንም ተጠቃሚ አደረጉ የሚል የተደራጀ መረጃም ሊኖረን ይገባል፡፡

አንድ ችግኝ፣ ዘር ከመምረጥ እስከ ማፍላት ያለው ሒደት በገንዘብ ሲሰላ እስከ አንድ መቶ ብር ድረስ ወጪ ይወጣበታል፡፡ ይህ ለአንድ ችግኝ ሲሆን፣ የሁሉም ሲሰላ ወጪው ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አይከብድም፡፡ ያ የተተከለው ችግኝ አልጸደቀም ማለት ደግሞ ምን ያህል ወጪ እንደወጣበት ማስላቱ ከባድ ነው። እንኳን ይህ ሁሉ ገንዘብ ወጥቶበት የሚባክን ነገር ቀርቶ ኢትዮጵያ እንዲሁም ሀብት የሌላት አገር ናት፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነቱ ክፍተት በሁለተኛው ዙር እንዳይደገም ማድረጉ ትልቅ ብልህነት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን የመንግስትን ዩኒቨርሲቲዎችን ብቻ ስንወስድ 46 ያህል አሉን። በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በትንሹ እስከ 10 ሺ ተማሪዎች አሉ እንበል፡፡ እነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ተማሪዎቻቸውን ይቀልባሉ፡፡ የሚያበስሉት ደግሞ በእንጨት ነው፡፡ የምግብ ማብሰያ እንጨት የሚመጣው ደግሞ ደን እተጨፈጨፈ ነው፡፡ የደን ሳይንሱን በአግባቡ ያውቃል የሚባለው የወንዶ ገነት የደን ኮሌጅ ራሱ የሚያበስለው ከደን በሚሰበሰብ ማገዶ ነው። ከዚህ ባሻገር የተለያዩ ማረሚያ ቤቶች የሚያበስሉት አብዛኞቹ በማገዶ ነው፡፡ ገጠርም ከተማም ያሉ እንዲሁ የሚያበስሉት በማገዶ ነው፡፡

ይህን ሊቀለብስ የሚችል ነገር ደግሞ የታቀደ ኮሜርሻል ፕላንቴሽን ወይም ለንግድ የታቀደ ሰው ሰራሽ ደን ነው፡፡ ይህ በልዩ ትኩረት መታቀድ አለበት፡፡ በደርግ ዘመነ መንግስት ተጀምሮ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት የተፈጥሮ ሀብቱን መጠበቅ እንደተጠበቀ ሆኖ ጎን ለጎን ለማገዶም ሆነ ለኮንስትራክሽን ለምሳሌ ለኤሌክትሪክ ምሰሶ ከሚያስፈልገው ጀምሮ የሚያገለግል ተብሎ ታቅዶ መተከል አለበት፡፡ እስካሁን ይህ የለም፡፡ ነገር ግን ታቅዶ መሰራት አለበት፡፡ ይህን ለመስራት ደግሞ የባለሙያም ችግር የለብንም፡፡ ልምዱም አለን፡፡ በዚህ ላይ በሁለተኛው ዙር በትኩረት ቢሰራበት የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አረንጓዴ አሻራ ሲባል ችግኞች እንዲተከሉ የሚታሰቡት ገላጣና በጣም የተጎዳ መሬት ላይ ነው፤ ለም በሆነ መሬት ላይስ ለምን አይተከልም?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** የምንሰራው የማዳበር ስራ ከሆነ በገላጣ ቦታ ብንተክል ችግር የለውም፡፡ በተፈፈጥሮ የግጦሽ አሊያም የሳር መሬት የሆነውን ወደግጦሽ መቀየር ስህተት ነው፡፡ ይህ ሆነ ማለት ጤናማ በሆነ መሬት ውስጥ ባዕድ ነገር እንደማስቀመጥ ይቆጠራልና እሱ ደግሞ ሲሆን ስርዓቱን አናጋናው ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በተፈጥሮ የእርሻ መሬት የሆነው ላይ ባህር ዛፍ መትከል ወይም በሌላ አገላለጽ ማሳን ወደባህር ዛፍ በታ መቀየር በጣም አደገኛ ነው፡፡ ሲሆን ሲሆን ተዳፋት የሆነ መሬት ላይ ችግኞችን ብንተክል ተመራጭ ነው፡፡ ዋናው አገራዊ ችግራችን የደን፣ የሳር፣ የእርሻ መሬት እያልን አለመለየታችን ነው፡፡ በዚህ መልክ ያለመለየታችን የአቅም ችግር አይመስለኝም፡፡ አሁንም ቢሆን ምርታማነቱ እንዲቀጥል ከተፈለገ ይህ መስተካከል አለበት፡፡

ከዚህ አኳያ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲም ሕግም የለንምና እሱን በማውጣት ደኑ ወደግብርና ሲሄድ መከልከል፤ ግብርናም ወደ ደኑ ሲሄድ መከልከል ያስፈልጋል፡፡ የደኑን መሬት ግብርናው ጨፍጭፎ ወደአዝርዕትነት ለመቀየር ሲታገል ሕግ ሊኖር ይገባል ባይ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አገር በቀል ችግኞችን ለማግኘት ዋጋ እንደሚያስከፍል ይነገራል፤ ከዚህም የተነሳ የውጪው ላይ ርብርብ ሲደረግ ይስተዋላል፡፡ ስለዚህ መፍትሔው ምንድን ነው ይላሉ?**



**ዶክተር ገመዶ፡-** ለዚህ ችግሩ ችግኝ ስለመተከሉ ሩጫ የሚጀመረው ሰኔ ሲቃረብ መሆኑ ነው፡፡ አገር በቀል ዝርዎች አብዛኛዎቹ በመደብ ላይ ከአንድ ዓመት በላይ መቆየትን የሚፈልጉ ናቸው፡፡ የበጀት ዓመቱ በሚጀምረው ሐምሌ ላይ እቅዱ ሲታቀድ ከነሐሴ ጀምሮ ዘሮቹ ካሉበት ተፈልገው መፈላት መጀመር ግድ ይላቸዋል፡፡ ስለዚህ አገር በቀል ዝርያዎች ነው የምንተክለው ብሎ ያቀደ አመራር በየችግኝ ጣቢያዎች እንዲፈሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የግል ችግኝ ጣቢያ ያሏቸው ተቋማት የውጭ ዝርያዎች ፈጥነው እስከ ስድስት ወር ድረስ ስለሚደርሱላቸው የሚያዘጋጁቸው እነርሱን ነው፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆንና የተሻለውን ውጤት ለማምጣት መልፋት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ግን አገር በቀል ችግኞችን ብቻ መትከል የተሳሳተ ስለሚሆን ያንን ብቻ ማድረግ አይጠበቅብንም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ የችግኝ ተከላውን ወደቀጣናው አገር በማስፋት ላይ ትገኛለች፤ ይህንን የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዴት እያስተዋለው ነው?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** ሁለት ነገሮችን መለየት አለብን፤ በፖለቲካው በኩል የታየነው እንዴት ነው የሚለው ነገር ሲጤን የታየነው በጣም በመልካም መንፈስ ነው። ለምሳሌ ኮትዲቯር የራሳቸው የግሪን ሌጋሲ ኢኒሼቲቭ አላቸው፡፡ ሩዋንዳን ስናይ ደግሞ በተለይ በጽዱነቷ ለዓለም አቀፉም ማኅበረተሰብ ምሳሌ የሆነች አገር ናት፡፡

በዚሁ ግለት ግን ኢትዮጵያ አንድ ለየት ያለ እድል ያላት እና ያልተጠቀመችበት ብዬ የምለው ተራራዎችን ወደማሳነት ቀይሮ ስርዓት ምህዳሩን ለአደጋ ከማጋለጥ መቻል አለብን፡፡ እንደሚታወቀው ጎረቤቶቻችን ስናይ ዝቅ ያሉ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ኢትዮጵያ ከፍ ያለች አገር ናት፡፡ አረብ አገሮችን ጨምሮ ደኖቻችንን በአግባቡ አድምተን እንዲሁም የውሃ መገኘትን ጨምረን ውሃን ኤክስፖርት የማድረግ እቅድ ቢያዝ ትልቅ የኢኮኖሚ ትርጉም ያለው ስራ መስራት ይቻላል፡፡

ለምሳሌ የአረብ አገራት፣ ሁለቱም ሱዳኖች ውሃን የሚያኙት ከየት ነው? ኢትዮጵያ የውሃ መገኛነቷ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ይህን ምቹ እድል መጠቀም ያለብን በሐሳብ ሳይሆን ታቅዶ መሆን አለበት፡፡ እንዲህ ስናደርግ ጉዳዩን ከቢዝነስ ጋር ማገናኘት ቻልን ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ውሃንም አልምተን ለውጪ ገበያ ማቅረብ እንችላለንና ቢታሰብበት መልካም ነው፡፡ በአጠቃላይ ግን ኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ የአካባቢውን አገራት ለማስተሳሰር የምታደርገው ጥረት የሚበረታታ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አገር ውስጥ ያሉ ዝርያዎችን በተመለከተ ከብዝሃ ሕይወት አኳያ ሲታያይ ምን ያህል አቅም አለ ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** የውጭ ዝርያዎችንም ሆነ የአገር ውስጥ ዝሪያዎችን የምንተክለው በአግባቡ ባህሪያቸውን ተረድተን ቢሆን ተጠቃሚዎች እንሆናለን። በውጭ ቴክኖሎጂ ላይ ብቻ ማተኮር አገራዊ ልማትን አያረጋግጥም። አገራዊ ልማት የሚሳለጠው አንድም ከራስ በመነጨ አቅም ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ አንደኛ ዝርያዎቻችንን በአግባቡ መለየት አለብን፡፡

ኢትጵዮያ በብዝሃ ሕይወት ሀብቶቻቸው በጣም የበለጸጉ ናቸው ከተባሉ 25 አገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ ይህ መታደል ነው፡፡ ይህ በየትኛውም መስፈርት ኢትዮጵያ ጥሩ አገራት ናት ተብሎ የሚሰጠን አሊያ የተሰጠን ነገር ሳይሆን በተፈጥሮ የታደለች አገር ሆና ያገኘችው ነው፡፡ የብዝሃ ሕይወት መገኛ ደግሞ ደንና ረግራጋማ (ዌትላንድ ወይም የመሬት ኩላሊት) አካባቢዎችን በአግባቡ በመያዝ ነው፡፡ ረግራጋማ አካባቢዎች ደግሞ በርካታ የብዝሃ ሕይወት ሀብቶቻችን መገኛ ናቸውና እያንጣፈፉ ወደማሳነት መቀየር ኪስራ ነው፡፡ ይህን አሰራር ትልልቅ የመንግስት ኃላፊዎች እንደስኬት የሚያወሩት መሆን የለበትም፡፡

እያንዳንዱ የብዝሃ ሕይወት ሀብት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው፤ ከመድሃኒት አኳያ ሲታይ ወደ ስድስት ሺ 29 አካባቢ ዝርያዎች አሉን፤ ከዚያ ውስጥ 10 ከመቶ የመድሃኒት እጽዋዕት ናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ የመድሃኒት ፋብሪካዎችን እንገንባ ብንል እንኳ በአግባቡ ከለየንና ከተጠቀምንበት አቅማችን ብዙ ሊያስኬደን የሚችል ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ያሉ ተመራማሪና በመንግስት በኩል ጥሩ የሆነ ተግባቦት መኖር አለበት፡፡ ተመራማሪው ሁሌ ተቺ መሆን የለበትም፤ መንግስትም ተመራማሪውን ከቁምነገር የማይቆጥር መሆን የለበትም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣናው ያለው የአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ውህደት እውን የሚሆነው የተፈጥሮ ሀብቶችንና ድንበር ተሻጋሪ ስነ ምህዳሮችን በጥንቃቄ በማስተዳደር ነው ይባላል፤ ይህን እንዴት ያዩታል**

**ዶክተር ገመዶ፡-** ይህ የግድ ነው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በከፍተኛ ደረጃ የፈጠሩት ድባብ በጣም ምቹ ነው። ኢትዮጵያ ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ እየጎላ ነው፡፡ እኛ ብቻ እየጠበቅን በሌላው አገር የሚኖር ተነሳሽነት የማይኖር ከሆነ ግን ትርጉም የለውም፡፡ በጋራ ለማደግ ድንበር ተሻጋሪ የተፈጥሮ ሀብት ማኔጅመንት (ትራንስባውንደሪ ናቹራል ሪሶርስ ማኔጅመንት) በደኑም ሆነ በውሃ መሰረታዊ ጉዳይ ነውና እሱ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ኢትዮጵያ ደግሞ በሁሉም አቅጣጫ እድሉም አላት፡፡

ጥሩ ነገሩ ኢጋድ ይህንን እንደ አንድ ትልቅ አንኳር ጉዳይ ይዞ እየተነሳ መገኘቱ ነው፡፡ በኢጋድና በሌሎች ተቋማት ቅንጅት የተሻለ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡ የተጀመረውም ችግኞችን የማጋራት እና አብሮ የመትከል ነገር ይህንን የበለጠ የሚያጠናክር ያደርጋልና ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ጫናን ለመቆጣጠር ምን ያህል ጥረት እያደረገች ነው?**

**ዶክተር ገመዶ፡-** ኢትዮጵያ በሁሉም መልክ ጥሩ የሚባል ስራ ስትሰራ ቆይታለች፡፡ አንደኛ እያደጉ ያሉ አገራት አፈ ጉባኤ ሆና ስታገለግል ቆይታለች፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ምሳሌ በመሆን እየመራች ትገኛለች፡፡ ለተፈጥሮ ሀብት መጥፋት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለመከላከል በከፍተኛ ደረጃ እየተሰራ ነው ያለው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ደግሞ የተከሰተ እና የቆየ ስለሆነ ዛሬ በምንተክለው ችግኝ ልንቀለብሰው የምንችለው ሳይሆን ጊዜ የሚፈልግ ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ በዚህ ላይ ስትራቴጂ አውጥታ እየሰራች ነው፡፡ በማላመድና በማሻሻል ላይ እየሰራች ትገኛለች፡፡ ይህ ደግሞ ጥሩ ምሳሌ የሚያደርጋት ናት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሙያዊ ማብራሪያ ከከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶክተር ገመዶ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**እያንዳንዱ የብዝሃ ሕይወት ሀብት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው፤ ከመድሃኒት አኳያ ሲታይ ወደ ስድስት ሺ 29 አካባቢ ዝርያዎች አሉን፤ ከዚያ ውስጥ 10 ከመቶ የመድሃኒት እጽዋዕት ናቸው። ከዚህ የተነሳ የመድሃኒት ፋብሪካዎችን እንገንባ ብንል እንኳ በአግባቡ ከለየንና ከተጠቀምንበት አቅማችን ብዙ ሊያስኬደን የሚችል ነው**

# ዓለም አቀፍ

## ዩክሬን የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ መጀመሯን ዜሌንስኪ አረጋገጡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዩክሬን በሩሲያ ጦር ላይ እፈጽመዋለሁ ብላ ስትዘጋጅበት የቆየችው እና ብዙ የተጠበቀው የመልሶ ማጥቃት ኦፕሬሽን መጀመሩን የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜሌንስኪ አረጋገጡ።

ፕሬዚዳንቱ ማረጋገጫ ከመስጠታቸው በፊት ዩክሬን የመልሶ ማጥቃት ኦፕሬሽኗን ስለመጀመሯ መረጃዎች ሲወጡ እንደነበር ቢቢሲ ዘግቧል።

የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲንም ከቀናት በፊት «የዩክሬናውያኑ መልሶ ማጥቃት ተጀምሯል» ብለው ነበር።

ይሁን እንጂ የመልሶ ማጥቃቱ ኦፕሬሽን ስለመጀመሩ ቀደም ብሎ ከዩክሬን ፕሬዚዳንት ማረጋገጫ አልተሰጠም ነበር።

«የመልሶ ማጥቃት እና የመከላከል እርምጃዎች እየተከናወኑ ነው» ያሉት ዜሌንስኪ፤ የኦፕሬሽኑ ደረጃንም ይሁን ይዘት በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ከመስጠት ተቆጥበዋል።

የዜሌንስኪ ማረጋገጫ የተሰማው በደቡብ እና ምሥራቅ ዩክሬን በሁለቱ ኃይሎች መካከል የሚደረገው ጦርነት ተፋፍሞ በቀጠለበት ወቅት ነው።

የዩክሬን ወታደሮች ረዥም ርቀት ሚሳኤሎችን እያስወነጨፉ በባክሙት ምሥራቅ አቅጣጫ እንዲሁም ከዛፖሬዢያ በቅርብ ርቀት በደቡብ አቅጣጫ ወደፊት እየገፉ ነው የሚሉ ሪፖርቶች ከዩክሬን ወገን እየወጡ ነው።

ይህ ይባል እንጂ በአውደ ውጊያው እየተከናወነ ያለውን በትክክል ማወቅ አዳጋች ነው። ሁለቱም ወገኖችን እርስ በእርሱ የሚጣረስ ሪፖርት ሲያወጡ ቆይተዋል። ዩክሬናውያኑ በመልሶ ማጥቃት ወደፊት እየገፉን ነው ሲሉ ሩሲያውያኑ ደግሞ የዩክሬንን ጥቃት እያከሸፍን ነው ይላሉ።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን አርብ ዕለት በተሰራጨ ቪዲዮ ላይ ሲናገሩ፤ የዩክሬን መልሶ ማጥቃት መጀመሩን ገልጸው፣ የሩሲያ ኃይል በዩክሬን ጦር ላይ ከፍተኛ



ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዜሌንስኪ

ጉዳት አስከትሎ መልሶ ማጥቃቱን እያከሸፉ እንደሆነ ተናግረዋል።

ለዚህ የፑቲን ንግግር ምላሽ በሚመስል መልኩ ፕሬዚዳንት ዜሌንስኪ ንግግር ሲያደርጉ፤ ፑቲን ማን እንደሆኑ እንደማያውቁ ለማስመሰል ትከሻቸውን ሰበቅ፤ ቅንድባቸውን ደግሞ ከፍ አድርገው፤ ሩሲያውያኑ ከአሁን በኋላ ‘ብዙ እንደማይቀራቸው’ መገንዘባቸው ጥሩ ነገር ነው ሲሉ ተደምጠዋል።

ዜሌንስኪ የአገራቸው ጦር መሪዎች ጥሩ መነቃቃት ላይ ናቸው ካሉ በኋላ «ይህን ለፑቲን ንገሩት» ብለዋል።

ዜሌንስኪ ይህን መልዕክት ያስተላለፉት ከካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ነው። በዚህ የሁለቱ መሪዎች ውይይት ላይ ካናዳ 500 ሚሊዮን ዶላር አዲስ የጦር ድጋፍ ለዩክሬን እንደምታደርግ ይፋ አድርገዋል።

ከመሪዎቹ ንግግር በኋላ የወጣው የጋራ መግለጫ ሁኔታዎች ሲፈቅዱ ዩክሬን በተቻለ ፍጥነት የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) አባል እንድትሆን ካናዳ ትደግፋለች ይላል።

የዩክሬን መልሶ ማጥቃት ዘመቻ ተጀምሯል ከተባለ በኋላ ከፍተኛ ውጊያ እየተካሄደባቸው ካሉ አካባቢዎች መካከል አንዱ ደቡባዊ ዛፖሬዢያ ነው። የሩሲያ መሪዎች እንደሚሉት ከሆነ የዩክሬን ጦር አዞቫ የተባለ የውሃ አካልን በቁጥጥራቸው ሥር በማድረግ የሞስኮን ኃይል ሁለት ቦታ ለመቁረጥ ጥረት ላይ ናቸው።

ባለፈው ሳምንት ኖቫ ካህኮቭካ የተባለው ግድብ እንዲወድም መደረጉ የፈጠረው የውሃ መጥለቅለቅ በዩክሬን መልሶ ማጥቃት ኦፕሬሽን ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ተገምቷል።

የፈረሰው ግድብ ያስከተለው መጥለቅለቅ 596 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ቦታን የሸፈነ ሲሆን ከ3ሺህ በላይ ሰዎች መፈናቀላቸው ተመላክቷል።

ኖቫ ካክሆቭካ በተሰኘውና በደቡባዊ ዩክሬን በሚገኘው የኃይል ማመንጫ ግድብ ላይ በደረሰ ጉዳትና መደርመስ ምክንያት አካባቢው በውሃ በመጥለቅለቁ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ቤታቸውን ለመልቀቅ እንደተገደዱ ተገልጾ ነበር።

እ.እ.አ በ1956 ዓ.ም በኒፕሮ ወንዝ ላይ የተገነባው ይህ ግድብ ለአካባቢው በርካታ ከተሞችና ለክሬሚያ ጭምር የመጠጥ ውሃ ምንጭ ሲሆን ለዛፖሪዥህ የኑክለር ጣቢያ ማቀዝቀዣ ውሃ የሚያገኘውም ከዚሁ ግድብ ነበር።

ግድቡ በምን ምክንያት ሊደረመስና ውሃው ሊፈስ እንደቻለ እስካሁን በትክክል ባይታወቅም፤ ዩክሬን ግን ፈጥና ድርጊቱ የሩሲያ የአሸባሪነት ድርጊት ነው ስትል ነው ለዓለምአቀፉ ኅብረተሰብ አቤት ያለችው።

የመንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክርቤት አስቸኳይ ስብሰባ በድርጅቱ የዩክሬን ተወካይ አምባሳደር ሰርጊየ ክይስሊይትስያ ባሰሙት ንግግር፤" በዩክሬን ሲቪሎች ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳት እንዲደርስ ታስቦ የተፈጸመ የሽብር ጥቃት ነው» ሲሉ ሩሲያን ወንጅለዋል።

የሩሲያው አምባሳደር ቫሲልይ ኔቤንዚያ በበኩላቸው፤ «በኪየቭ የተፈጸመና የጦር ወይም የሽብር ወንጀል ሊሰኝ የሚችል ደባ ነው በማለት እሳቸውም በፈንታቸው ዩክሬንን ወንጅለዋል። በጸጥታው ምክር ቤት የፈረንሳይና አሜሪካ ተወካዮች ድርጊቱን በማውገዝ እንዲጣራ በማሳሰብ አንዳቸውንም ግን በተጠያቂነት ሳይጠቅሱ አልፈዋል።

የአውሮፓ ህብረትና የኔቶ አባል አገሮች በያሉበት ሩስያን ተጠያቂ ሲያደርጉ ነው የተሰሙት። የአውሮፓ ካውንስል ፕሬዚዳንት ቻርለስ ሚሸል በትዊተር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት ድርጊቱ ከጦር ወንጀል የሚቆጠር ነው በማለት ሩሲያን ከሰዋል።

የሰሜን አትላንቲክ ጦር ቃል ኪዳን ድርጅት ኔቶ ዋና ጸሐፊ ሚስተር ስቶንቴንበርግም፤ በግድቡ ላይ የደረሰው ጉዳት ሩሲያ በዩክሬን ላይ እየፈጸመች ያለውን የጭካኔ ጥግ የሚያመላክት ነው ያሉት፡፡

«የካክሆቭካ ግድብ ውድመት በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ለችግር የሚዳርግና በአካባቢው ላይም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ነው» በማለት ድርጊቱ የሚያበሳጭና ሩሲያ በዩክሬን ጦርነት የምትፈጽመው ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ነው ማለታቸው ይታወሳል።

የጀርመኑ መሪ ቻንስለር ሹልዝ በሰጡት አስተያየትም ጥቃቱ ሩሲያኖች ዩክሬን በሩሲያ ላይ ልትወስድ ያሰበችውን የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ ለማስቆም የወሰደችው እርምጃ ሊሆን ይችላል በማለት፤ ይህም ሌላው የጦርነቱ አካል ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።


በሌላ በኩል ግን ዩክሬን ሩሲያን ለማጋለጥና ድጋፍ ለማግኘት እራሷ ግድቡ ላይ ጥቃት ፈጽማ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት የሰጡ አሉ።

ሌሎች ደግሞ ግድቡ እድሜ ጠገብ በመሆኑንና አሁን ደግሞ በጦርነት ምክንያት ክትትልና ጥገና ሳይደረግለት ስለቆየ ከውስጥ በተፈጠረ ጉዳት በራሱ ፈንድቶ ሊሆን ይችላል በማለትም የሚከራከሩ አሉ።

ሁሉም ታዛቢዎችና ተንታኞች ግን ችግሩ ከጦርነቱ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተያያዘ መሆኑን ይስማማሉ።

ረጅም ወራትን ያስቆጠረው የሩሲያና ዩክሬን ጦርነት በርካታ ውድመት እያደረሰ መሆኑን የዘገቡት ዶቼቬሌ እና ቢቢሲ ናቸው።

# ስፖርት



## የኢትዮጵያ ብስክሌት ቻምፒዮና በመቀሌ ይካሄዳል

**አስማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ ብስክሌት ቻምፒዮና በትግራይ ክልል መቐለ ከተማ እንደሚካሄድ የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡ ፌዴሬሽኑ ውድድሩን ለማካሄድ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም ገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን ከሚያካሂዳቸው ዓመታዊ የውድድር መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ የኢትዮጵያ ብስክሌት ቻምፒዮና ነው፡፡ ይህ ውድድር ዘንድሮ በትግራይ ክልል መቐለ ከተማ የሚካሄድ ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ የብስክሌት ማህበር የተመዘገበም ነው። ቻምፒዮናው እንደሁልጊዜውም ብሄራዊ ቡድኑን የሚወክሉ ብስክሌተኞች የሚመረጡበት እንደሆነም ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡ ውድድሩ ምንም እንኳን ዓመታዊ ቻምፒዮና ቢሆንም በክልሉ በጦርነት ምክንያት የተጎዳውንና ተቀዛቅዞ የሚገኘውን የብስክሌት ስፖርት ወደ ቀድሞ እንቅስቃሴው እንዲመለስ እና እንዲነቃቃ ታስቦ የሚደረግም ነው፡፡

ፌዴሬሽኑ ቻምፒዮናውን ለማካሄድ ዝግጅቱን ከትግራይ ክልል ብስክሌት ፌዴሬሽን ጋር እየሰራ እንደሚገኝም አስታውቋል፡፡ ውድድሩን የማዘጋጀት ዕድሉ ለሁሉም ክልሎች የተሰጠና ክልሎችም የማዘጋጀት ፍላጎት ቢኖራቸውም ካለው ሁኔታ አንጻር እድሉ ለትግራይ ክልል እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ክልሉ ውድድሩን ለማካሄድ በጸጥታው ረገድ ኃላፊነት የወሰደ ሲሆን፤ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝና በሰላም እንዲጠናቀቅም አረጋግጧል፡፡

ቻምፒዮናው ከሰኔ 14-18 2015 ዓ.ም ድረስ




የሚካሄድ ሲሆን፤ ከተለያዩ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና ክለቦች በሁለቱም ጾታ ከ170 እስከ 200 ብስክሌተኞች የሚሳተፉም ይሆናል፡፡ በሶስት የእድሜ እርከኖች ተከፍሎ ሁለት ዓይነት ውድድሮችም ይስተናገዱበታል፡፡ አንደኛው የውድድር ዓይነት የግል ሰዓት ሙከራ፤ ሁለተኛው ደግሞ የጎዳና ውድድር ነው፡፡ የዕድሜ እርከኖቹም አዋቂ፣ ወጣት እና ከ23 ዓመት በታች በሚል ተከፋፍሏል። በግል የሰዓት ሙከራ ተወዳዳሪዎች በየ ሁለት ደቂቃ ልዩነት የሚለቀቁ ሲሆን፤ ብቻቸውን እየጋለቡ በምን ያህል ሰዓት እንደሚጨርሱ ሙከራ ይደረጋል፡፡

በአዋቂ ወንዶች የግል ሰዓት ሙከራ 30 ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ የወጣት ወንዶች የግል ሰዓት ሙከራ ደግሞ 20 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ይሆናል። በአዋቂ ወንዶች ምድብ የጎዳና ውድድር 120 ኪሎ ሜትር፣ በወጣት ወንዶች 100 ኪሎ ሜትር ይሸፍናል፡፡ በአዋቂ ሴቶች ምድብ የጎዳና ውድድር 80 ኪሎ ሜትር፤ የግል ሰዓት ሙከራ ደግሞ 20 ኪሎ ሜትር ነው፡፡ በሴት ወጣቶች ምድብ የጎዳና ውድድር 60 ኪሎ ሜትር ሲሆን የግል ሰዓት ሙከራም 10 ኪሎ ሜትር ይሆናል፡፡ ርቀቱ እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር አሊያም ሊቀንስ ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍጹም ሞላ፤ የክልሉ ብስክሌት ፌዴሬሽንም ሆነ ተወዳዳሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለስፖርቱ ካበረከቱት አስተዋጽኦና በተለያየ ጊዜ ብሄራዊ ቡድኑን በመወከላቸው በትግራይ መቐለ ከተማ ለማካሄድ በስራ አስፈጻሚ መወሰኑን ይጠቅሳሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከክልሉ ብስክሌት ፌዴሬሽን ጋር ንግግር ከተደረገ በኋላ ለማዘጋጀት ኃላፊነት ሊወስዱ ችለዋል፡፡ ቻምፒዮናው በትግራይ ክልል መካሄዱ ትልቅ ፋይዳ ያለው ሲሆን፤ የተሻለ የብስክሌት እንቅስቃሴ ሲደረግበት የነበረ እንደመሆኑ ለብስክሌት ስፖርት እድገት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ማድረግ ችሏል፡፡

‹‹ብስክሌት በትግራይ ባህል ነው›› የሚሉት ኃላፊው ‹‹በሁለት ዓመቱ ጦርነት ብስክሌት ስፖርት ተጎድቷል። በክልሉ እንዲካሄድ የተወሰነውም ይሄንን ለማነቃቃት ነው፡፡ ውድድሩ ሲካሄድ በክልሉ ያሉ ክለቦችና ፌዴሬሽኑ ተነቃቅተው ወደ ቀድሞ እንቅስቃሴ እንዲመለሱ ታስቦ እንዲዘጋጅ ተወስኗል፡፡ በክልሉ ስፖርቱ ከፍተኛ ተወደጅነት ስላለው ጥሩ ዝግጅት እንደሚኖር እምነቴ ነው›› ብለዋል፡፡

በውድድሩ የሚያሸንፉ ተወዳዳሪዎችም ውጤታቸው በዓለም አቀፉ የብስክሌት ማህበር ድረ ገጽ ላይ የሚለጠፍ ይሆናል፡፡ የብስክሌት ስፖርት በባህሪው የድምር ውጤት በመሆኑ ለኦሊምፒክ፣ ዓለም ቻምፒና እና አፍሪካ ቻምፒዮና ለመሳተፍ ከሚደመሩት አንዱ ውድድር ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ቻምፒዮና የብሄራዊ ቡድን መመረጫ ውድድር ነው፡፡

በተለያዩ አገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን ተወዳዳሪዎችም በቻምፒዮናው ለመሳተፍ ወደ አገር ውስጥ እየገቡ መሆኑን የተነገረ ሲሆን፤ በተለያዩ የዓለም ክለቦች በስፔን፣ ፈረንሳይ በጣሊያንና አሜሪካ ክለቦች የሚወዳደሩ ኢትዮጵያውያን ብስክሌተኞች ይገኙበታል፡ ፡ በመሆኑም ጥሩ የውድድር ጊዜን በማሳለፍና ብሄራዊ ቡድኑን የሚወክሉ ብስክሌተኞች ተመርጠው ለዓለም አቀፉ የብስክሌት ማህበር በማስተላለፍ ውድድሩ እንደሚቋጭም ፌዴሬሽኑ አስታውቋል፡፡